ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 105 ታኅሣሥ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ስኳር ፋብሪካዎች
## የሀገር ውስጥ ፍጆታን መሸፈን ለምን አቃታቸው?

**ሞገስ ጸጋዬ**

ኢትዮጵያ 85 በመቶ የስኳር ፍጆታዋን ከውጭ ታስገባለች፡፡ በ2015 ዓ.ም እንደ ሀገር ማምረት የተቻለው 1 ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ወንጂ በዓመት አንድ ሚሊዮን ኩንታል የማምረት አቅም ቢኖረውም እያመረተ ያለው ከ300 እስከ 350 ሺህ ኩንታል ስኳር ብቻ ነው፡፡ አርጆ ደዴሳ የስኳር ፋብሪካ እያመረተ አይደለም፡፡ ጣና በለስ፣ ኦሞ ኩራዝ ሦስትና ፊንጫ እያንዳንዳቸው በዓመት 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ስኳር የማምረት አቅም ቢኖራቸውም

ስኳር ፋብሪካዎች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## በሌማት ትሩፋት
### ከ5 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተትና ከ3 ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት ተገኝቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሌማት ትሩፋት መርሀ-ግብር በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት አምስት ቢሊዮን 726 ሊትር ወተት፣ 328 ነጥብ ሁለት ሺህ ቶን ስጋ፣ 96 ነጥብ ሰባት ሺህ ቶን ማርና ከሶስት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት መገኘቱን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ ዮሐንስ ግርማ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የቤተሰብ ብሎም በሀገር ደረጃ የምግብ

በሌማት ትሩፋት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የንግዱ ማኅበረሰብ ግብሩን በአግባቡ ሊከፍል ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የንግዱ ማኅበረሰብ ግብሩን በአግባቡ ሊከፍል እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።


በመዲናዋ ከየወረዳው የንግድ ማኅበረሰብ ጋር ሲደረግ የነበረው ውይይት ትናንት በሚሊኒየም አዳራሽ የማጠቃለያ መድረኩ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተገኙበት ተካሂዷል።

የውይይቱ ተሳታፊ ነጋዴዎች በበኩላቸው፤ ሕገ-ወጥ የጎዳና ላይ ንግድ ሕጋዊ ነጋዴውን ገቢ ከማቀጨጩም በላይ የከተማዋን ገፅታ እያበላሸ መሆኑን ጠቅሰው፤ ጠንካራ ክትትል እንዲደረግ፣ የግብር ትመና በተጠና መልኩ እንዲወሰን እና የደረሰኝ አሰጣጥ ሥርዓቱ ላይ በርካታ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ አንስተው፤ የከተማ አስተዳደሩ ችግሮቹን ሊቀርፍ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የጋራ ተጠቃሚነትን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ከንቲባ አዳነች አቤቤ



## በሐረረ
አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል

ገጽ 6

















አቶ ደስታ ለገሰ

# በክልሉ በወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ800 ሺህ ብር በላይ ማዳን ተችሏል

- ከአንድ ነጥበ 8 ሚሊዮን በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በአምስት ወራት ውስጥ በወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ800 ሺህ ብር በላይ ማዳን መቻሉን የሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሴቶች ፣ወጣቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሴቶች፣ ወጣቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የወጣቶች ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደስታ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በተያዘው በጀት ዓመት አምስት ወራት ውስጥ በተሠራ ወጣቶች በጎ ፍቃድ ሥራ ይወጣ የነበረ 823 ሺህ 324 ብር በላይ ማዳን ተችሏል፡፡

በዚህም በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ከአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ብር በላይ በወጣቶች በጎ ፍቃድ ለማዳን የታቀደ መሆኑን አስታውቀው፤ በአምስት ወራት ውስጥ የእቅዱን 63 በመቶ የሚሆነውን እንደተገበረ አቶ ደስታ ገልጸዋል፡፡

በዚህም በበጀት ዓመቱ የወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት 612 ሺህ 76 ወጣቶችን በክረምት እና 142 ሺህ 279 ወጣቶችን የበጋ አገልግሎት በአጠቃላይ 754 ሺህ 156 ወጣቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ እስካሁን 698 ሺህ 667 ወጣቶች መሳተፋቸውን አስታውቀዋል፡፡

በየዓመቱ በሚተገበረው ይህ አገልግሎች በተያዘው በጀት ዓመት በአጠቃላይ ከ2 ነጥብ 3 በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ በአምስት ወራት ውስጥም 1 ሚሊዮን 847 ሺህ 754 የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አቶ ደስታ ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በዚህ መርሀ ግብርም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር፣የጤና አገልግሎት ፣ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ጨምሮ ፣የቤት እድሳት ፣አቅመ ደካሞችን ማገዝ፣ የማዕድ ማጋራት እና በመሳሰሉት በ13 ተግባራት ላይ የሚሳተፉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አቶ ደስታ ወጣቶች በበጎ ተግባራት ላይ መሳተፋቸው የማኅበራዊ እሴቱን ከማጎልበት አንፃር ያለው ሚና የጎላ ነው። በዚህም ማኅበረሰቡ በጎ ፈቃድን ልማድ እያደረገ ወጣቱም በብዛት እየተሳተፈ እና ኅብረተሰቡም ተጠቃሚ እየሆነ ነው ብለዋል፡፡

ወጣቱም በእንደዚህ ዓይነት መልካም ተግባራት በመሳተፍ በጎነትን ልማድ ማድረግ እና ማኅበራዊ ኃላፊነቱን መወጣት ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# በሐረሪ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ሳስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



አዲስ አበባ፡- በሐረሪ ክልል በሩብ ዓመቱ በ26 የኢንቨስትመንት መስኮች ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ መግባታቸው ተገለጸ።

በክልሉ የኢንቨስትመንት ቢሮ ዳይሬክተር አቶ ሰሚር ሬድዋን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሩብ አመቱ 24 ባለሀብቶችን ለማስተናገድ ታቅዶ ለ26 ባለሀብቶች ፈቃድ መስጠት ተችሏል። በእቅዱ ባለሀብቶቹ ከ350 ሚሊዮን ብር በላይ ያስመዘግባሉ ተብሎ የተጠበቀ ቢሆንም ከእቅዱ በላይ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ አስመዝግበው ወደ ሥራ ገብተዋል።

የተሰማሩባቸው መስኮችም በማኑፋክቸሪንግ አራት፤ በሆቴል አራት ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ አስራ ስምንቱ ገበያ፤ ጤና እና ትምህርትን በመሳሰሉ የአገልግሎት ዘርፎች እንደሆነም ጠቁመዋል።

ይህም ሆኖ ከዚህ በፊት በነበረው ሂደት በከፍተኛ የገንዘብ መጠን ለኢንቨስትመንት ተመዝግበው ወደ ሥራ ያልገቡ ባለሀብቶች ነበሩ ያሉት አቶ ሰሚር፤ አንዳንዶችም ለኢንቨስትመንት በሚል የተሰጣቸውን መሬት እየሸነሸኑ እስከመሸጥ ደርሰው ነበር ብለዋል።

በመሆኑም ካለፈው ዓመት ጀምሮ መስራት የሚችሉትን ለመለየት ካስመዘገቡት ገንዘብ ቢያንስ ሰላሳ በመቶ በባንክ መኖሩን የማረጋገጥ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። በዘንድሮው ሩብ ዓመትም ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች 400 ሚሊዮን የሚደርስ ብር በባንክ እንዳላቸው የተረጋገጠላቸው ናቸው ብለዋል።

በእነዚህ 26 ፕሮጀክቶች ከአንድ ሺህ በላይ ቋሚ እንዲሁም በግንባታ ወቅት ሁለት ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥሩ ይሆናል። በቋሚነት በሚፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ ከሚሆኑት መካከል 35 በመቶ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም በክልሉ በቂ ሙያተኛ ካልተገኘ በምሥራቅ ኦሮሚያ ካሉ አካባቢዎች ጋር በመነጋገር ለኢንቨስትመንቱ የሰው ሀብት ለማሟላት የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

በሌላ በኩል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ ያልገቡ ስምንት ኢንቨስተሮች ፈቃዳቸው መነጠቁን የጠቆሙት አቶ ሰሚር፤ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች የተሰማሩ 37 ባለሀብቶች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል ብለዋል።

ፈቃዳቸው የተነጠቁት ወዲያውኑ በሚመለከተው አካል በኩል የወሰዱት መሬት እንዲመለስ የሚደረግ ሲሆን፤ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውም በሚጠበቀው ደረጃ ወደ ሥራ ካልገቡ ተመሳሳይ እርምጃ የሚወሰድባው ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል።

በአጠቃለይ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የክልሉ ዳያስፖራዎች ተሳትፎ አበረታች እንደሆነ የተናገሩት አቶ ሰሚር፤ ነገር ግን ከከተማ ኢንቨስትመንት ባለፈ በተለያየ መስክ መሳተፍ የሚፈልጉ የክልሉ ተወላጆች እንዳሉም ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም በኢንቨስትመንት ቢሮው በኩል በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋርና ሌሎች ክልሎችም በሚፈልጉት ዘርፍ እንዲሰማሩ ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸው እንደሆነ ጠቁመው፤ ከተማዋ የቱሪዝም ማእከል እንደመሆኗ በአገልግሎት ዘርፍ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም አዳዲስ ለሚመጡ ባለሀብቶች ቦታና ሌሎች አገልግሎቶችን ከማቅረብ ባለፈ ቢሮውን ከባንክ ጋር በማገናኘት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

# የአትክልት ዋጋ እየናረ በመምጣቱ መቸገራቸውን ሸማቾች ተናገሩ

## -ንግድ ቢሮ በበኩሉ በቂ ምርት እንዲገባ እየሠራ መሆኑን አስታውቋል

**አመለወርቅ ከበደ**



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የአትክልት ገበያ ዋጋ በየጊዜው እየናረ መምጣቱንና የምርት እጥረት መኖሩንም ሸማቾች ተናገሩ:: ምርት በስፋት ለማስገባት ከአርሶ አደሮች እና ማህበራት ጋር በትስስር እየሠራ እንደሚገኝም የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ገልጿል::

ከስድስት ኪሎ አትክልት ተራ ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ኤልሳቤት አሰፋ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአትክልት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው::

ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነገረው ምርት በስፋት መግባት አለመቻሉ ነው ያሉት ወይዘሮዋ፤ ምርት በስፋት እንዲገባ ቢደረግ መልካም ነው:: አሁን ባለው የዋጋ ሁኔታ መሸመት የማይችሉ በርካታ ነዋሪዎች እንዳሉም ሊታሰብ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል::

ሌላኛው ሸማች አቶ ግርማ ወንድሙ በበኩላቸው፤ አሁን ያለው የአትክልት ዋጋ ከባለፈው ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ቢሆንም፤ የአትክልት ዋጋ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ስለሆነ፤ አቅርቦት ላይ በስፋት ቢሠራ መልካም ነው ሲሉ ገልጸዋል::

በተጨማሪም ትዕግስት ሀብቴ የተባሉ ሸማች በበኩላቸው፤ አሁን ላይ ሽንኩርት ከነበረበት ዋጋ ቀንሶ 110 ብር የሆነ ቢሆንም፤ በዚህ ዋጋ ገዝቶ መብላት የማይችል ብዙ ሰው ስላለ አቅርቦቱና ዋጋው ላይ ቢሠራበት መልካም ነው ብለዋል::

በስድስት ኪሎ አካባቢ የሚሰሩት አቶ ሸመልስ ፍቃዱ እንደገለጹት፤ የምርት አቅርቦት ሳይኖር ሲቀር ወይም አንድ እና ሁለት ቦታ የሚገኝ ከሆነ ምርቱ ያደረ እንኳን ቢሆን ዋጋ ጨምሮ የመሸጥ ሁኔታ አለ::

ለምርት አቅርቦት ችግር እንደ ምክንያት የሚነሳው አቅራቢዎች ለደላላ ሁለትና ሶስት ቦታ እንደሚከፍሉ እና መንገድ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዳሉ የጠቀሱት አቶ ሸመልስ፤ የአቅርቦት ችግር መኖሩ እና የዋጋ ጭማሪው የአትክልት ገበያው እንዲዳከም አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል::

አሁን ላይ በዋጋም በጥራትም መሻሻል እንዳለ የተናገሩት አቶ ሸመልስ፤ ሽንኩርት ከ105 እስከ 110፣ ድንች 28፣ ካሮት 50 እስከ 55፣ ቲማቲም 70 ብር እየተሸጠ እንደሚገኝ አስረድተዋል::

ከንግድ ቢሮ ጉብኝት የሚያደርጉ ሰዎች ሲመጡ ይወረሳል የሚል ስጋት ስላለ ለሁለትና ሶስት ቀናት እቃ የማይገባበት ሁኔታም እንዳለ በመጥቀስ፤ በዚህ ረገድ በግቢው የተዋቀሩ ኮሚቴዎች ስላሉ እነሱ አውርደው ዋጋ የማረጋጋት ሥራ ቢሠሩ እና እውነተኛ የሆኑ ሰዎች ቦታ ተሰጥቷቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ቢያቀርቡ ሊሻሻል ይችላል ሲሉ ተናግረዋል::

አቶ ካሊድ አብዱራህማን በበኩላቸው፤ የአትክልት ውድነት መኖሩን በመጥቀስ ለዚህም እንደ ምክንያት ያነሱት የአቅርቦት እጥረት እንዳለ ነው:: ለዚህም መንግሥት ከገበሬው ጀምሮ ቢሠራ መልካም ነው ብለዋል::

በአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በምርት አቅርቦት ላይ ያጋጠመውን ችግር ለመፍታት ከገበሬዎች እና ከሌሎች ተቋማት ጋር እየተሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ ሕገወጥ ደላሎችን የመቆጣጠር ሥራም እየተሠራ ነው::

የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያን በተመለከተ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን አለ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ችግሩን ለመፍታት ንግድ ቢሮ እየሠራ ነው ብለዋል::

ለአቅርቦት ችግር ምክንያት የሆነው የሕገወጥ ደላሎች ጣልቃ ገብነት፤ ምርቶቹ በተፈጥሮ በቶሎ የሚበላሹ በመሆናቸው በሚጓጓዙበት ወቅት የመበላሸት ሁኔታ ስላለ በርካታ ምርት ይባክናል ሲሉ አስረድተዋል::

አቶ ሰውነት እንደገለጹት፤ ቢሮው ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ ባለፉት ግዜያት ሶስት መቶ ከሚሆኑ ከተለያዩ አርሶ አደሮች እና ማህበራት ጋር በቀጥታ ምርት እንዲያቀርቡ ለማድረግ ስምምነት ተፈራርሟል::


በተጨማሪም የከተማ ግብርናን ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ የምርት ብክነትን ለመከላከል በተለያዩ ቦታዎች የአትክልት ማከማቻ እና መሸጫ ማዕከላትን በመገንባት እንደምርቱ ባህሪ ማስቀመጫ ቦታ በማዘጋጀት እንዳይበላሹ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል ሲሉ ጠቅሰዋል::

ዜና

# በአምስት ወራት 100 የዓይን ብሌን ተለግሶ፤ 181 የዓይን ብሌን ቃል ተገብቷል

## - የዘርፉ ሐኪሞች ቁጥር 11 ብቻ መሆኑ ችግር ፈጥሯል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ 100 የዓይን ብሌን ልገሳ መደረጉንና 181 ሰዎች የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል መግባታቸውን የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ በሀገሪቱ ያሉ የዓይን ንቅለ ተከላ ሀኪሞች ቁጥር 11 ብቻ መሆኑ በዘርፉ ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡

የኢትዮጵያ የደምና ህብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዓይናቸውን በብሌን ጠባሳ ምክንያት አጥተው ለዓይነ ስውርነት የተጋለጡ ዜጎችን ብርሀን ለመመለስ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት 108 የዓይን ብሌን ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ 100 የዓይን ብሌን የተለገሰ ሲሆን፤ ይህም ለጤና ተቋማት መሠራጨቱን አቶ ሀብታሙ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ 208 ዜጎች የዓይን ብሌናቸውን እንዲለግሱ ቃል ለማስገባት ታቅዶ፤ 181 ሰዎች የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል ገብተዋል ብለዋል፡፡

የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል የሚገቡ ሰዎች ቁጥር ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሻሻል ማሳየቱን ገልጸዋል፡፡

ባለፈው ዓመት 12 ወራት ውስጥ ከ190 ያልበለጡ ዜጎች የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል መግባታቸውን አንስተው፤ በተያዘው ዓመት በአምስት ወር ብቻ 181 ሰዎች ቃል መግባታቸውን አስታውቀዋል፡፡

ህልፈት ካጋጠመ በኋላ የዓይን ብሌንን መለገስ ባህሉ ያደረገ ማኅበረሰብ ለመገንባት ለነገ የማይባል ተግባር ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ የዓይን ብሌን ልገሳ ለለጋሹ በህይወት ዘመኑ የመንፈስ እርካታ እንዲሰማው ያደርጋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የዓይን ብሌን ልገሳ የብሌንን አካላዊ ፋይዳ በማሳወቅ የዓይን ብሌን ለጋሽ ቁጥር እንዲጨምር ይደረጋል ብለዋል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት የዓይን ብሌን ስብሰባና ልገሳ ሥራ በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰነ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ የክልል ደም ባንኮች ወደ ተግባሩ እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በክልሎች በሚገኙ ደም ባንኮች የሚገኙ ተጠሪ ሰዎችን በማሰልጠን የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች በየአካባቢያቸው ቃል መግባት የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠሩን አስረድተዋል፡፡



አቶ ሀብታሙ ታዬ

በሀገሪቱ የዓይን ንቅለ ተከላ አገልግሎት እየተሰጠ ያለው በአዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ መቀሌ፣ ጅማ እና ሀዋሳ ብቻ ናቸው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ የሐኪሞቹም ቁጥር 11 ብቻ በመሆናቸው የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ የሚፈልጉ ሰዎች ተደራሽ መሆን አልቻሉም ብለዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁለቱም ዓይናቸው በዓይን ጠባሳና ተያያዥ ምክንያት ለዓይነ ስውርነት የተጋለጡ 300 ሺህ በላይ ሰዎች መኖራቸውን ጥናት አጣቅሰው ተናግረዋል፡፡

የዓይን ብሌን ተለግሷቸው እይታቸው የተመለሰላቸው፣ ቃል የገቡ ሰዎች፣ የመምህራንና የእምነት ተቋማት ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ የሚፈጥሩበት መድረክ እንደሚዘጋጅ አመላክተዋል፡፡

የዓይን ብሌን ለጋሾች ቁጥርን ለመጨመር የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙም ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

በተለይ በክልል ከተሞች የዓይን ብሌን ስብሰባና ልገሳ ሥራ የሚከናወንባቸው ማዕከሎችን የማስፋፋት ሥራም እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

የሕክምና ባለሙያዎችን ቁጥርን የማሳደግ እና የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ትኩረት መስጠቱንም አብራርተዋል፡፡

የዓይን ብሌን ልገሳ ከህልፈት በኋላ የሚደረግ በመሆኑ ለለጋሹ ጉዳት የሌለው በህይወት ለሚኖረው ግን ብርሃን መሆኑን በመረዳት ኅብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በስልጤ ዞን ከ145 ሺህ ኩንታል በላይ የበርበሬ ምርት ተሰበሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ ዞን በ2015/16 ዓ.ም የመኸር እርሻ ከ145 ሺህ ኩንታል በላይ የበርበሬ ምርት መሰብሰብ መቻሉን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

የስልጤ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙርሰል አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በበጀት ዓመቱ በ2015/16 ዓ.ም የመኸር እርሻ በዞኑ ከ145 ሺህ ኩንታል በላይ የበርበሬ ምርት ተሰብስቧል፡፡

በ2015/16 የመኸር እርሻ ስምንት ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት ላይ በርበሬ ለማልማት ታቅዶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሙርሰል፤ ስምንት ሺህ 288 ሄክታር በማልማት የእቅዱን 104 በመቶ መፈፀም መቻሉን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ሙርሰል ገለጻ፤ ምርታማነቱ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከ40 ሺህ ኩንታል በላይ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

የመኸር እርሻው በመሬት ሽፋንም ሆነ በምርትና ምርታማነት ጭማሪ አሳይቷል ያሉት ኃላፊው፤ በመሬት ሽፋን 140 ሄክታር ጭማሪ መታየቱንም አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በ2014/15 የመኸር እርሻ በምርት ትመና በሄክታር 14 ነጥብ አምስት የነበረው ወደ በ2015/16 የመኸር እርሻ 17 ነጥብ ስድስት ከፍ ማድረግ መቻሉን አቶ ሙርሰል ጠቁመዋል፡፡

የገበያ ትስስር ችግርና በበርበሬ በሽታ ምክንያት የምርት መቀነስና ገበሬው በርበሬ የማምረት ፍላጎት ቀንሶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሙርሰል፤ በ2015/16 መኸር እርሻ ዘሩ በኬሚካል ታሽቶ በመዘጋጀቱ በምርታማነቱ ላይ አወንታዊ ሚና መጫወቱን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ሙርሰል ገለጻ፤ በመኸር እርሻው 25 ሺህ 524 አርሶ አደር ተሳትፏል፡፡ በተጨማሪም ከዘር እስከ ገበያ ማቅረብ ድረስ ባለው ሂደት ለብዙ ዜጎች በጊዜያዊነት የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

የገበያው ትስስሩ ለማሳደግ በላንፉሮ ወረዳ ጦራ ከተማ ላይ ትልቅ የበርበሬ ገበያ ማዕከል ተቋቁሞ የሎጅስቲክስ ሥራውን በማሳለጥ በቀጥታ ነጋዴዎች ከአርሶ አደሩ የሚገዙበት መንገድ መፈጠር መቻሉን አቶ ሙርሰል ተናግረዋል፡፡

በቀጣይም ተሞክሮው በሌሎች ከተሞች በማስፋት አርሶ አደሩን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉና የተደራጁ የገበያ ማዕከላት ለመገንባት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በቀጣዩ መኸር እርሻ የግንዛቤ ክፍተቶችን በመቅረፍ ከዘጠኝ ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በርበሬ ለማልማት መታቀዱንም አንስተዋል፡፡

# 150 ሺህ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ዲጂታል መታወቂያዎች ወደ ሀገር ገብተዋል

**ዳግማዊት አበበ**

ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት

Public Service Transport Service

አዲስ አበባ ፡- የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት 150 ሺህ ዲጂታል መታወቂያዎችን ወደ ሀገር ማስገባቱን አስታወቀ። በሁለት ወር ውስጥ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ይሆናል ተብሏል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የአይቲ ዳይሬክተር አቶ ቃልኪዳን ገበየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅ እንደገለጹት፤ ዲጂታል መታወቂያው የኤንኤፍሲ (NFC) ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ሲሆን፤ ይህም መታወቂያው ያለ ምንም ንክኪ በሴንሰር እንዲሰራ ያደርገዋል።

ይህ ዲጂታል ካርድ ከዚህ ቀደም አገልግሎት ሲሰጥ የነበረውን የወረቀት መታወቂያ ላይ ያሉትን ችግሮች የሚቀርፍ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም የቀድሞ መታወቂያ በቀላሉ መታተም የሚችል በመሆኑ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየገጠመ ያለውን የፎርጂድ መታወቂያ መስፋፋት የሚያስቀር ነው ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ መታወቂያው ዲጂታል ነው ሲባል የአንድን ሰው ሙሉ መረጃ የሚይዝ ነው። በአውቶቡሶቹ ላይም ካርዱን የሚያረጋግጥ ሶፍት ዌር የሚገጠም መሆኑን ገልጸው፤ የካርድ ማረጋገጫው ወይም “ቫሊዴተሩ” ተገልጋዩ ዲጂታል ካርዱን ይዞ ወደ አውቶቡሱ በሚቀርብበት ወቅት ሙሉ መረጃውን የሚያወጣና የሚተነትን ይሆናል ብለዋል ። ተገልጋዩ የያዘው ካርድ ትክክል ካልሆነም ድምጽ በማውጣት ልክ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል።

ካርዶቹን የሚያነብ ሶፍት ዌር እየለማ ያለው ዘፕሪሚየም ኢትዮጵያ በተሰኘ ሀገር በቀል ድርጅት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በየጊዜውም ካርዶቹ ላይ ሙከራ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ካርዶቹ ከጥራትም ሆነ ከጥንካሬ አንጻር ቢተጣጠፉ እንኳን የማይሰበሩ በመሆናቸው ተገልጋዮች ካርዶቹን ከአስር ዓመት በላይ እንዲጠቀሙባቸው ታስቦ የተሰራ ነው።

ካርዱ በሀገሪቱ ያለውን የወረቀት ፍጆታ በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ በተጨማሪም የቁጥጥር እና አገልግሎት ቀልጣፋነትን የሚጨምሩ ናቸው ብለዋል ።

መታወቂያዎቹ የመንግሥት ሠራተኛው ከትራንስፖርት አገልግሎት በተጨማሪ እንደ ኤቲኤም(ATM) ካርድ ብር በመሙላት ሌሎች አገልግሎቶችን መፈጸም እንዲችል የሚያደርጉ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰዓት ታትመው ወደ ሀገር የገቡት 150 ሺህ ካርዶች ከሁለት ወር በኋላ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ይሆናሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዚህ ዓመትም የሙከራ ሥራውን በማጠናቀቅ በቀጣዩ ዓመት ሙሉ በሙሉ ወደ ትግበራ ለማስገባት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጋራ አደጋ የሆነውን ወንጀል በጋራ መከላከል ይገባል

የሰው ልጅ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም እንቅስቃሴና መስተጋብሮቹ ሰላማዊ ሆነው በሰላም እንዲከናወኑለት ይሻል፡፡ ይሁን እንጂ ሁልጊዜ እንዳሰበውና እንደተመኘው ወጥቶ ላይመለስ፣ ሰርቶም ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡፡ ይሄ የሰው ልጅ ወጥቶና ሰርቶ በመግባት ሂደት ውስጥ በዚህ መልኩ የሚገጥሙት እክሎች ደግሞ ከወንጀል ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

ወንጀል በተለያየ መልክና ደረጃ የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ሊፈጸም የሚችል ነው። ከግል ቂምና ያልተገባ መሻት ጀምሮ፣ ከተራ ሌብነት ከፍ እስካለው የሰው ልጆችን ሕይወት እስከመንጠቅ የሚደርሱ በብዙ ገጻቸው የሚዘረዘሩ የወንጀል ተግባርና ዓይነቶች አሉ፡፡ እነዚህ ወንጀሎች ጊዜንና ሁኔታን ማዕከል አድርገው ሊቀንሱ አልያም ሊበራከቱ የሚችሉበት እድልም ስለመኖሩ በርካታ ማሳያዎችም አሉ፡፡

ለወንጀል መበራከት እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀሰው የሰላም መደፍረስና ግጭት ነው፤ በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ከተራ ሌብነት ጀምሮ፣ ዘረፋ፣ ሕገወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ፣ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ እንዲሁም የጅምላ ፍርድን የመሳሰሉ የወንጀል ተግባራት ሲፈጸሙ ይስተዋላል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም በተለይ በበዓላት ሰሞን እና ሕዝባዊ ሁነቶች በሚኖሩባቸው አጋጣሚዎች እነዚህ ወንጀሎች ይበራከታሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም አሁን ላይ በአንድ በኩል ሰላምና አለመረጋጋቱ፡፡ በሌላ በኩል የበዓላትና ሕዝባዊ በዓላት ድባቡ እየተቃረበ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የመከሰቻ ምቹ ሁኔታዎች በአንድ የሚገጣጠሙ ናቸው። በዚህም የወንጀል ተግባራት ሊበራከቱ እንደሚችል ይገመታል፡፡ የሰላም መደፍረሱ ለወንጀለኞችና ሕገወጦች እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ ከመሆኑ ባሻገር፤ በዓላትና ሕዝባዊ ሁነቶች ሲደመሩበት ወንጀለኞች ሕዝብን መስለው ለመንቀሳቀስም፤ ግርግሩንም ለወንጀሉ ማሳለጫ ለመጠቀምም ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

የሰሞኑ የጉምሩክ ኮሚሽንም ሆነ የፖሊስ ኮሚሽን መረጃዎች በዚህ ረገድ የሚጠቁሙት ሃቅ አለ፡፡ ለምሳሌ፣ በተለያየ ጊዜ የሚወጡ የፖሊስ መረጃዎች እንዳመለከቱት፣ በኮትሮባንድና ሕገወጥ ንግድ ዝውውሩ ሂደት ከውጭ የሚገቡም፣ ወደ ውጭ የሚወጡም እቃዎች አሉ፤ ከነዚህ ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መድኃኒት፣ የጦር መሳሪያዎች፣ ተተኳሾች፣ ምግብ ነክ እቃዎች፣ አልባሳት፣ ኮስሞቲክስ፣ የተለያዩ የውጭ ሀገራት ገንዘቦች፣ እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ይሄን መሰል ሕገወጥ የወንጀል እንቅስቃሴ ደግሞ በማህበረሰቡ ጤና፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ብሎም ሰላምና ደህንነት ላይ ከፍ ያለ አደጋን የሚፈጥር ነው፤ ይሄንን ተግባር ለመከላከልም ፖሊስ ከአጋር ተቋማት ጋር እንዲሁም በኅብረተሰቡ ትብብር ታግዞ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ከሰሞኑም የፌዴራል ፖሊስ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽኖች በጋራ በሰሩት የኦፕሬሽን ሥራ ከአንድ ሺህ የሚልቁ ተጠርጣሪዎችን ከነሕገወጥ ቁሳቁሶቻቸው በቁጥጥር ስር ማድረጋቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

ፖሊስ ኮሚሽኖቹ በጋራ በሰጡት መግለጫ መሠረት፤ የኅብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በማወክ ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ ከአንድ ሺ በላይ የሆኑት እነዚህ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር በዋሉበት ወቅት፤ ለሕገወጥና ወንጀል ተግባራቸው የሚጠቀሙባቸው አራት ሽጉጦች፣ 68 የሽጉጥ ጥይት፣ አምስት ልዩ ልዩ መኪኖች፣ 64 የተሽከርካሪ ሰሌዳዎች፣ 1461 ልዩ ልዩ የተሽከርካሪ ዕቃዎች፣ ሶስት ባጃጅ፣ አንድ ጀነሬተር፣ 290 ሞተር ሳይክሎች፣ ስምንት ፔዳል ብስክሌቶች አብረው ተይዘዋል።፡

ከእነዚህ በተጨማሪም 31 ሺህ የአሜሪካን ዶላር፣ 1578 ልዩ ልዩ የሞባይል ስልኮች፣ 52 ታብሌት፣ 71 ላፕቶፕ፣ 12 ኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያ ስታብላይዘር፣ 58 ልዩ ልዩ የዲሽ ዕቃዎች፣ 48 ቴሌቪዥን፣ 44 ሲምካርድ፣ 10 የመንገድ ፍሳሽ ማስወገጃ የብረት ክዳን፣ ሁለት በግራይንደር፣ ከ5ኪሎ ግራም በላይ ካናቢስ አደንዛዥ ዕፅ፣ 1292 የሺሻ ማስጨሻ ዕቃዎች እና 153 ልዩ ልዩ አልባሳት እንዲሁም በግለሰብ ቤት ተከማችቶ የነበረ ለግብይት የሚያገለግሉ 90 ከረጢት የኢትዮጵያ ሳንቲሞች በተመሳሳይ በኢግዚቢትነት ተይዘዋል፡፡

በተመሳሳይ በኦፕሬሽኑ 37 ቁማር ቤቶች እና 3241 የቤቲንግ ቤቶች የታሸጉ ሲሆን፤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቤት ውስጥ ጥይቶችን የሚያመርት አንድ ተጠርጣሪም ከ4052 የክላሽ ጥይት፣ 1297 ባዶ የክላሽ እርሳስና 1319 የክላሽ ቀለሀ ከሚያመርትበት ማሽኖች ጋር በቁጥጥር ስር ማዋል ተችሏል።

እነዚህ እና መሰል የወንጀል ድርጊቶች ታዲያ፣ ከግለሰብ እስከ ሀገር የሚያደርሱት ቀውስ ቀላል አይደለም። ሰዎች በልቶ የማደር፤ ሰርቶ ሀብት ንብረት የማፍራት፤ ወልዶ የመሳም፤ ሌላው ቀርቶ ወጥቶ የመግባት ሕልውናቸውን አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የወንጀል ድርጊቶች አደጋቸው የአንድ ወገን ሳይሆን የሁሉም እንደመሆኑ፤ ወንጀሉን የመከላከል ሂደትም ለአንድ ወገን የሚተው ሳይሆን የሁሉም ኃላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለምህረት የተዘረጉ እጆችን መቀበል ሀገርን ከጥፋት መታደግ ነው

**ዳንኤል ዘነበ**

እውቁ ግሪካዊ ጸሐፊ እና የታሪክ ሰው ሔሮዶቱስ የጦርነትን አስከፊነት " In peace, sons bury their fathers. In war, fathers bury their sons!" "በሰላም ጊዜ ልጆች አባቶቻቸውን ይቀብራሉ፤ በጦርነት ጊዜ አባቶች ልጆቻቸውን ይቀብራሉ" በሚል ገልጾታል። ይህም የጦርነትን እጅግ አስከፊ ገጽታን ብቻ ሳይሆን የሰላምን ጥቅምና አድማሳዊነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። በርግጥ ከመጣንበት መንገድ አንጻር የጦርነትን አስከፊነት፣ የሰላምን አቻ የለሽነት ከኢትዮጵያዊያን በላይ የሚያውቀው አለ ብሎ መናገር ይከብዳል።

ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት እርስ በእርስ ተዋግተን አይተነዋል። ይህም ሆኖ ከትናንቶቻችን መማር ባለመቻላችን፣ ዛሬም ከጦርነት አዙሪት አልወጣንም። ለሁለት ዓመት በዘለቀው የትግራይ ጦርነት ከፍተኛ ዕልቂትና ውድመት ተፈጥሯል። አሁን የአማራ ክልልን ጨምሮ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ፍላጎታቸውን በጠብመንጃ አፈሙዝ ማስፈጸም የሚሹ ኃይሎች የሀገሪቱን ሰላም እየተፈታተኑ ነው።

እነዚህ ኃይሎች ውድ የሰላም አመራጮችን እንዲመለከቱ፣ ከኃይል አማራጭ ወጥተው ወደ ድርድርና ውይይት እንዲመጡ በተደጋጋሚ ጥሪዎች ቢቀርቡም ለጥሪው ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉም። ከአንዳንዶች ጋር /ከአሸባሪው ሸኔ / የተለያዩ ድርድሮችን ረጅም ርቀት ተሄዶ ቢደረግም ውጤታማ መሆን አልተቻለም።

በየትኛውም ሀገር በትጥቅ የታገዘ አለመግባባትና ግጭት እጅግ ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ካስከተለ በኋላ በዘላቂነት ሲቋጭ በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ሳይሆን በሰላማዊ ውይይት እና ድርድር ነው። የዓለም ታሪክ እንደሚያስረዳውም ጦርነት ለሰላም በተዘረጉ እጆች እንጂ በመሣሪያ እጦት አይቆምም ።

በተለይ አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ለሰላም ሃሳብን በሃሳብ ከማሸነፍ የተሻለ አማራጭ የለም፤ ዘላቂ ሰላም ማምጣት የሚቻለውም በሰላማዊ ድርድር፣ በምህረት እና በይቅር ባይነት ነው። ይህንን አለመገንዘብ ከሁሉም የከፋ ጊዜን የሚዋጅ አስተሳሰብ የማታጥ አልፋና ኦሜጋ ነው።

ደም አፋሳሹ የትግራይ ጦርነት ብዙ ጉዳትን ካስከተለ በኋላም ቢሆን በሰላማዊ ድርድር ተቋጭቶ አዎንታዊ ውጤትን አሳይቶናል።

የለውጥ ኃይሉ ወደ ስልጣን ከመጣ ማግሥት ጀምሮ /ከዛም በፊት/ ይሄንኑ በመገንዘብ ለሀገራችን ሰላም ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ አይዘነጋም። በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል /በትግራይ ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሃይማኖት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና እናቶችን ያካተተ ቡድን የሰላም መንገድ ጠራጊ አድርጎ ተንቀሳቅሷል።

ወደ ጦርነት ከተገባም በኋላ ቢሆን መንግሥት ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ታግሶ፣ ስለሰላም ጥሪዎችን ሲያቀርብ ነበር። በጦርነቱ የኃይል ሚዛኑ በእጁ በሆነበት ጊዜም ቢሆን፤ ጦርነቱ በሰላም ስምምነት ቢቋጭ ሀገርን አትራፊ የሚያደርግ መሆኑን አምኖ የፕሪቶርያው የሰላም ስምምነት እንዲፈረም ትልቁን ድርሻ ተጫውቷል ፡፡

በትግራዩ ጦርነት መንግሥት በዚህ ደረጃ ሆደ ሰፊ ሊሆን የቻለው በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት/ መንፈስ የተቋጩ ጦርነቶች ዘላቂ ሰላም እንደማያሰፍኑ ከመገንዘብ ብሎም፤ ሰላምን ለማጽናት ካለው ብርቱ ፍላጎት አንጻር እንደሆነ ይታመናል። ከተግባሩም መረዳት የምንችለው ይሄንኑ ነው።

በዚህም በትግራይ ክልል ለሁለት ዓመት የቆየውን ጦርነት በሰላማዊ ስምምነት በመቋጨቱ የትግራይ ሕዝብ እናቶች እንባ ታብሷል። መንግሥት ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ከማድረግ ካለው ኃላፊነት አንጻር ችግሮችን በሆደ ሰፊነት በድርድር ፣ በምህረት ለመፍታት የሄደበት ርቀት ውጤት አስገኝቷል።

ይህም ደም አፋሳሹን የትግራይ ጦርነት በማስቆም ረገድ ተጨባጭ ለውጥ አምጥቷል። በዚህም የመንግሥትን ሰላም ፈላጊነት ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሳይቀር በተግባር አይተነዋል። ውጤቱ ምንም ይሁን ምን፤ እንደ ፕሪቶርያው ሁሉ ከአሸባሪው ሸኔ ጋር ያለውን አለመግባባት በውይይት ለመፍታት ወደ ታንዛኒያ ዳሪሰላም በመጓዝ ሰላምን ፍለጋ ባዝኗል።

መንግሥት ቀደም ባሉት ጊዜያት ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ከሃሳብ ይልቅ በጠብመንጃ ለማስፈጸም ተደራጅተው 'ዱር ቤቴ ' ካሉት ቡድኖች ጋር ለመነጋገር ተደጋጋሚ ጥሪ አድርጓል። በዚህም በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል፣ በኦሮሚያ ፣ በሱማሌ ፣ በአማራ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ በርካታ የታጠቁ ኃይሎች የተዘረጉላቸውን የሰላም እጆች ተቀብለው ወደ ማኅበረሰቡ በመቀላቀል መደበኛ ሕይወታቸውን እየኖሩ ይገኛሉ።

እነዚህ ለሰላም የተዘረጉ የመንግሥት እጆች ዛሬም አልታጠፉም። ከመንግሥት ባህሪ አንጻር መቼም ሊታጠፉ እንደማይችሉ መገመት የሚከብድ አይሆንም፤ ለዚህም ከሰሞኑ በአማራ ክልል ለወራት የዘለቀውን የሰላም እጦት ለመፍታት መንግሥት ለታጠቁ ኃይሎች ጥሪ ማድረጉ አንድ ተጨባጭ ማሳያ ነው ።

በክልሉ ለወራት የዘለቀው የሰላም እጦት ሕዝቡ የእለት ተእለት እንቅስቃሴውን በአግባቡ እንዳይመራ ችግር ፈጥሮበታል፤ በተለይ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ይበልጥ እንዲጎዱ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። የክልሉን ሕዝብ ነገዎች ተስፋ እያደበዘዘ ስለመሆኑም ለመናገር የሚከብድ አይደለም ።

በክልሉ ውስጥ ያለውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ መንግሥት ያቀረበው የሰላም ጥሪ የሕዝቡ ፍላጎቱ ጭምር እንደሆነ በተለያየ መልኩ ታይቷል። በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ሲካሄዱ በነበሩ የሰላም ውይይቶች የክልሉ መንግሥት የሰላም አማራጮችን በመዘርጋት ክልሉ ወደ ሰላም የሚመጣበትን መንገድ እንዲያረጋግጥም ኅብረተሰቡ ሲጠይቅ ተሰምቷል፡፡ መንግሥት ካለው የሰላም ፍላጎት እንዲሁም ከሕዝቡ ጥያቄ በመነሳት የሰላም ጥሪው ተደርጓል።

መንግሥት እንደ ትግራዩ ሁሉ ዛሬም የኃይል ሚዛኑ ቢኖረውም የሰላም እጆቹን በመዘርጋት ሆደሰፊነቱን እያሳየ ነው። ምክንያቱ ድብቅ አይደለም። ዘላቂ ሰላም ማምጣት የሚቻለው ችግሮቻችን በሰለጠነ ወይም በሰጥቶ መቀበል መርህ መፍታት ያስፈልጋልና ነው። በአውደ ውጊያ ከሚገኝ ድል ይልቅ በሰላማዊ ድርድር፣ በምህረት ፣ በይቅር ባይነት የሚገኘው ድል ኢትዮጵያን አሸናፊ ያደርጋታልና።

የሰላም ጥሪው ከሀገር አልፎ ለራሳቸው ለታጠቁ ኃይሎች የሚበጅም ነው፡፡ ስለሕዝብም ሲሉ ሰላምን እንዲመርጡና ምህረት እንዲደረግላቸው እድል የሚሰጥ ነው። አለመግባባቶች በንግግር እንዲፈቱ የሚያስችል ነው። የሰላም ጥሪው ግጭት እና ውድመት እንዲቆም፣ በማኅበረሰቡ መካከል መደማመጥ እንዲሰፍን እንዲሁም መረጋጋትና ልማት እንዲመጣ የሚያስችል ጭምር እንደሆነም ይታመናል።

መንግሥትም ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ መፍታቱ ሁሌም የተሻለ አማራጭ በመሆኑና የሕዝብን እፎይታ ከልብ በመሻት የሰላም ጥሪው ማድረግ መቻሉ ሆደ ሰፊነቱን ይናገራል። ከዚህም በላይ የጀመረውን የሕዝባችንን ሕይወት የመለወጥ /ድህነትን ታሪክ የማድረግ ፈታኝ ትግል ስኬታማ እንዲሆን ሰላም ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ስለመሆኑም ያለው ግንዛቤ ከፍ ያለ ነው። ከትናንት ስህተቶቻችን የመማሩንም ጉዳይ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ይህ የመንግሥት ስለ ሰላም ያለው ቁርጠኝነት፤ ከባህሪው የመነጨ ከመሆኑ አንጻር ከፍ ያለ እውቅና ሊሰጠውና ሊበረታታ የሚገባ ነው፤ ከግጭት አዙሪት የመውጫ ትልቁ /ዋነኛ መንገድ ስለሆነም እያንዳንዱ ዜጋ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ሊደግፈው ይገባል። የመጪውን ትውልድ እጣ ፈንታ የሚወስን ከመሆኑ አንጻርም የሁሉም ዜጋ ትኩረት ሊሆን ይገባል።

በተለይም በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች በመንግሥት የተደረገውን የሰላም ጥሪ የማይደገም እድል እንደሆነ በመገንዘብ አጋጣሚውን በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ለዚህ ምንም ዓይነት ምክንያት መፍጠር አይጠበቅባቸውም።

የመንግሥትን ጥሪ ተቀብሎ ፊትን ወደ ልማት ማዞር መቻል ሀገርን የሚያጸና እንጂ፤ አንገት የሚያስደፋ ተግባር አለመሆኑን መረዳት ይገባል። አያት ቅድም አያቶቻችን ዛሬ በኩራት ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራትን፣ በስሟ የምንምልባትን ሀገር አጽንተው ሊያቆዩልን የቻሉት፤ የሃሳብ ልዩነታቸውን በይደር፤ የሀገር ፍቅራቸውን በልባቸው አድርገው ነው። በመሳሪያ አፈሙዝ ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማስፈጸም የሚደረግ አካሄድ ሀገር አፍራሽ ነው። የሁላችንም ጎጆ ለሆነችው ሀገራችን / ኢትዮጵያ የሚበጅ አይደለም።

ዜና

# በተለያዩ አካባቢዎች ከ11 ሚሊዮን በላይ የአቮካዶ ችግኞች ተተክለዋል

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት አራት ወራት በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች 11 ሚሊዮን 53 ሺህ 917 የአቮካዶ ችግኞች መተከላቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። በበጀት ዓመቱ አራት ወራት ከሁለት ሺህ አራት ቶን በላይ የአቮካዶ ምርት ለውጭ ገበያ ተልኮ 682 ሺህ 468 በላይ የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

በግብርና ሚኒስቴር የሆልቲካልቸር ልማት ክፍል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብደላ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች 11 ሚሊዮን 53 ሺህ 917 የአቮካዶ ችግኝ በ58 ሺህ 699 ሄክታር ማሳ ላይ ተተክሏል።

በአቮካዶ ተከላው 352 ሺህ 418 ወንድና 39 ሺህ 570 ሴት አርሶ አደሮች መሳተፋቸውንና የእንክብካቤ ሥራዎች መቀጠላቸውንም አስረድተዋል።

በ2015/16 የምርት ዘመን 15 ሚሊዮን 874 ሺህ 795 የአቮካዶ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 14 ሚሊዮን 103 ሺህ 212 ችግኝ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

ቀሪ ያልተተከሉ ችግኞችን ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ማሳ ላይ ለመትከል አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አስረድተዋል።

የአቮካዶን የወጪ ንግድ ለማሳለጥ ላኪዎችና ክልሎች ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚረዳ የሎጂስቲክ



የአቮካዶ ችግኝ

ድጋፍ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሚገኝ አቶ አብደላ ተናግረዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ አራት ወራት ከሁለት ሺህ አራት ቶን በላይ የአቮካዶ ምርት ለውጭ ገበያ ተልኮ 682 ሺህ 468 በላይ የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

በበጀት ዓመቱ ሦስት ሺህ 170 ቶን የአቮካዶ ምርት ለመላክ መታቀዱን ያስታወሱት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ባለፉት አራት ወራት ሁለት ሺህ አራት ቶን በላይ አቮካዶ መላክ ተችሏል ብለዋል፡፡

አቶ አብደላ አክለውም፤ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2015/2016 የምርት ዘመን አራተኛ ወር ድረስ 13 ሺህ 849 ነጥብ 72 ቶን የአቮካዶ ምርት ለውጭ ገበያ በመላክ ከስድስት ሚሊዮን 207 ሺህ ዶላር በላይ ገቢ እንደተገኘ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ አብደላ ገለጻ፤በአራት ወራት ውስጥ ከአነስተኛ አርሶ አደሮች ማሳ የአቮካዶ ፍራፍሬ ምርትን በማሰባሰብ ከአማራ ክልል 20 ቶን የአቮካዶ ምርት ወደ ፈረንሳይ ተልኳል፣ ከሲዳማ ክልል ደግሞ 20 ነጥብ አምስት ቶን የአቮካዶ ዘይት ወደ ፖርቹጋል እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል 69 ነጥብ 25 ቶን የአቮካዶ ምርት ወደ ውጪ ሀገራት ተልኳል።

የአቮካዶ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለችግኝ ተከላው የሚሆኑ ምርጥ ዝርያዎችን የማባዛት ሥራ በሰፊው እንደሚከናወንም አመላክተዋል።

# በሌማት ትሩፋት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዋስትናን ለማረጋገጥ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዚህም በጀት ዓመቱ አምስት ወራት አምስት ቢሊዮን 726 ሊትር ወተት፣ 328 ነጥብ ሁለት ሺህ ቶን ስጋ፣ 96 ነጥብ ሰባት ሺህ ቶን ማርና ከሶስት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት ተገኝቷል ሲሉ አስተድተዋል።

የዶሮ ሥጋና የእንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ ነው ያሉት አማካሪው፤ በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት 88 ነጥብ ስምንት ሺህ ቶን የዶሮ ስጋ እንዲሁም 10 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የቆዳና ሌጦ ምርት መገኘቱም ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ዮሀንስ ገለጻ፣ የሌማት ትሩፋት ዋና ዓላማ በሀገሪቱ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በቤተሰብ ብሎም በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የአመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል ነው፡፡

የሌማት ትሩፋት የሥነምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ፣ ከውጭ የሚገባ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት እና የሥራ ዕድልን በመፍጠር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

በተጨማሪም የሕፃናትን መቀንጨር ለመከላከልና እንደሀገር ያለውን ሥርዓተ ምግብ ጤናማ ለማድረግ የሌማት ትሩፋት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

የማር ምርትን ከማሳደግ አኳያ የዘመናዊ የንብ ቀፎዎችን የማሰራጨት ሥራ ተሰርቷል ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ በአምስት ወራት 315 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች ለተጠቃሚዎች መሰራጨታቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪ የወተት ላም ዝርያ ማሻሻል በሌማት ትሩፋት ፕሮግራም በተለየ ትኩረት ከሚሰሩ ተግባራት መካከል አንዱ ሲሆን፤ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን የማቅረብ ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

የእንስሳት ጤና አገልግሎት ከማሻሻል አኳያ የክትባት አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አማካሪው፤ በዚህም የድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችን የመከላከል፣ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራን የመከላከልና ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ አዲስ የተያዙ አካባቢዎችን ከበሽታው የማፅዳት ሥራ መሰራቱን አብራርተዋል፡፡

የሌማት ትሩፋት አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩን እና ሸማቹን የሚያገናኝ ድልድይ ሲሆን፤ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች አበረታች ውጤት ማስገኘቱን አመላክተዋል።

# የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ ከንግዱ ማኅበረሰብ በተሰበሰበ ገቢ ብክነትን ያስቀረ ተጨባጭ ለውጦች የታዩባቸው ሥራዎች ማከናወን መቻሉን ጠቅሰው፤ የገቢ ግብርን በአግባቡ መክፈል እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

ከለውጡ በኋላ መንግሥት የሠራቸውን የልማት ሥራዎች ጠቅሰው፤ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን አስረድተዋል። በዚህም ከደረሰኝ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ መሠረታዊ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ ጠንካራ ክትትል ይደረጋል ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የንግዱ ማኅበረሰብ ግብርን በአግባቡ ሊከፍል ይገባል ብለዋል።

በመዲናዋ ከለውጡ በኋላ ከአንድ ሺህ 400 ኪሎ ሜትር በላይ አዳዲስ መንገዶች፣ አድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ፕሮጀክት፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የአንድነት ፓርክ፣ የእንጦጦ ፓርክ፣ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የእሁድ ገበያና ትልልቅ የገበያ ማዕከላት ተገንብተዋል። ይህንን ማድረግ የተቻለው በግብር ከፋዮች መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር አባይ በበኩላቸው እንዳስረዱት፤ ሕገ-ወጥ ንግዱን ለማስቀረት አስተዳደሩ የጀመራቸው ሥራዎች አሉ። በመርካቶ የሚገኘውን የንግድ ማኅበረሰብ በ33 ብሎክ በመከፋፈል ጠንካራ ክትትል ተደርጓል፤ በዚህም አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል።

ሕጋዊነትን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ አንዳንድ ሕጋዊ ነጋዴዎች ለትብብር ወደኋላ ሲሉ ተስተውሏል ብለዋል።

ችግሮችን በጋራ ለማረም የንግዱ ማኅበረሰብ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን አንስተው፤ ሕገወጥነትን የመከላከል ተግባር የሁሉም ኃላፊነት ነው ሲሉ ምክትል ከንቲባው አመላክተዋል፡፡

ሕጋዊ ነጋዴው ከመንግሥት ጋር የሚያደርገው ትብብር በመቀነሱ ችግሩ አሁንም ድረስ እንዲኖር ምክንያት ሆኗል። ስለዚህ ችግሩን ከሥር መንቀል እንደሚገባ ተናግረዋል።

መድረኩ የንግዱ ማኅበረሰብ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በማድመጥ መፍትሔ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣ የዘርፉን አገልግሎት ለማዘመን፣ የኑሮ ወድነትን ለመቀነስ፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣ ሕገ ወጥ ንግድን ለመከላከል፣ ሀገርን በጋራ ለማልማት እና የንግዱ ማኅበረሰብ የሚያጋጥሙትን ችግር ለመቅረፍ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል፡፡

# ስኳር ፋብሪካዎች የሀገር ውስጥ....

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚፈለገውን ያህል ምርት እያመረቱ አይደለም:: ለመሆኑ የስኳር ፍጆታችንን ማሟላት ያቃተን ለምንድነው?

መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአገዳ ግብዓትና የምርትና እጥረት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የጸጥታ ችግሮች ስኳርን በስፋት ለማምረት ትልቅ ፈተና ደቅነዋል:: ፋብሪካዎች ባላቸው ሙሉ አቅም እንዲያመርቱ የፖሊሲ ማዕቀፍ አለመኖሩ ትልቅ ችግር ደቅኖ ቆይቷል:: የአሰራር ክፍተት፣ ሌብነትና ማጭበርበር ሌላው የዘርፉ ፈታኝ ችግሮች ናቸው::

የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አብዱራህማን ኢድ ጣሂር እንደሚሉት፤ በመጀመሪያ የስኳር ዘርፉ ኢትዮጵያ ውስጥ ትርፋማና በጥሩ ሁኔታ ከሚነሱ ዘርፎች ውስጥ ዋነኛው ነበር:: ከ70 ዓመት በፊት ሲጀመር እንደ አየር መንገድ መስመር ይዞ በሶስት ፋብሪካዎች ብዙ ምርት ይመረት እንደነበር አስታውሰዋል::

የስኳር ምርት ዋነኛ ችግር የሸንኮራ አገዳ ምርት እጥረት ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ የፋብሪካዎችን ቁጥር ከ10 በላይ ለማሳደግ በተደረገው ሙከራ የስኳር ምርት በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል ይላሉ::

የሀገር ውስጥ ፍላጎት የሚሟላው 85 በመቶ ከውጭ በማስገባት ነው:: የወንጂ ስኳር ፋብሪካ በ2007 ዓ.ም ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስኳር አምርቶ ነበር:: አሁን ላይ ከ400 ሺህ ኩንታል በታች እያመረተ ይገኛል:: ይህ ሊሆን የቻለው በዋነኝነት በአገዳ ምርት ችግር ነው:: ወንጅ ስኳር ፋብሪካ 6 ሺህ ሄክታር መሬት ብቻ ነው ያለው:: የተቀረው ከገበሬዎች ጋር በሚኖር ውል መሠረት ነው የሚገኘው:: በዚህ ሂደት ላይ በተፈጠረው ክፍተት በአቅሙ ልክ ማምረት አለመቻሉና አርሶ አደሮች ሌሎች ምርቶችን ወደ ማምረት በመግባታቸው የአገዳ ምርት በመቀነሱ ስኳር ለማምረት ችግር ሆኗል::

ፋብሪካዎች በየዓመቱ ተፈተው በአዲስ መለዋወጫ መጠገን ይፈልጋሉ ያሉት አቶ አብዱራህማን፤ ፋብሪካዎችን ለመጠገን የተወሰኑ መለዋወጫ እቃዎች ከውጭ መምጣት አለባቸው:: ነገር ግን እንደ ሀገር ባለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ፋብሪካዎች ችግራቸው ባለመፈታቱ ምርት የማምረት ችግር ገጥሟቸዋል:: አሁን ሰባቱ ፋብሪካዎች የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ መደረጉንና የአገዳ ምርት የማስፋት ሃሳብ መኖሩን ገልጸዋል::

ከሰምና ወንጂ ፋብሪካዎች አገዳ የሚያስመርቱት በአርሶ አደሮች ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ይህም በተፈለገው ልክ ምርት እንዳያመርቱ አድርጓቸዋል:: ጣና በለስም የማሽነሪ ችግሩን መፍታት ይጠበቅበታል፤ አርጆ ደዴሳ በጸጥታ ችግር እያመረተ አይደለም፤ ከሰም ስኳር ፋብሪካ 80 በመቶ የአገዳ ግብዓት የሚያገኘው ከአርሶ አደሮች ነው:: የራሱ መሬት ትንሽ በመሆኑ በአገዳ እጥረት ምክንያት አያመርትም:: ፊንጫም ያለበትን ችግር በመቅረፍ ወደ ምርት እንዲመለስ ሙከራዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል::

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንትና የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አወሉ አብዲ በበኩላቸው፤ ያለፉት ጊዜያት ፋብሪካዎቹ ባላቸው ሙሉ አቅም እንዲያመርቱ የፖሊሲ ማዕቀፍ አለመኖሩ ትልቅ ችግር ነበር ይላሉ:: የተወሰነ የፖሊሲ ማዕቀፍ ቢኖርም ትግበራው ችግር ነበረበት:: ብዙ ጣልቃ ገብነቶች፣ የአመራር ድክመትና ውስንነት ነበረው:: እንዲሁም የድጋፍና የክትትል ውስንነት ነበር::

አገዳ የሚያቀርቡ አርሶ አደሮች ጋር ተያይዞ አርሶ አደሮች በአግባቡ ተጠቃሚ አለመሆናቸው ለወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሌላው ችግር ነበር ያሉት አቶ አወሉ፤ ከአገዳ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የመሬት ዝግጅትና እንክብካቤ፣ የማዳበሪያ፣ የውሃና ውሃ ፓምፕ መሰል ግብዓቶች ጋር ሲነጻጸር የተሰጠው ትኩረት አናሳ እንደነበርም ጠቅሰዋል:: የፋብሪካ ምርታማነት ቢኖርም ፋብሪካዎች በብዛት እንዲያመርቱ ከማድረግ አንጻር ሌብነትና የማጭበርበር ሁኔታዎች መኖራቸውንም ገልጸዋል::

በዚህም ከፍተኛ እዳ ውስጥ ገብቶ ከሞላ ጎደል ፋብሪካው የመቆም ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር በማስታወስ ከአስር በላይ የስኳር ፋብሪካዎች እየተገነቡ ነው የሚል የኢንዱስትሪ አብዮት የሚመስል ወሬ ነበር ብለዋል፤ ይሁንና ስኳሩ አልነበረም:: የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት አልተቻለም ሲሉ ተናግረዋል::

በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ያለውን ችግር ለመለየት ጥናት አድርገናል ያሉት የቦርድ ሰብሰቢው፤ ለምርት መዳከም የአመራር ችግር ዋናው እንደነበርም ጠቁመዋል:: ከላይ እስከታች ያለው አመራር ችግሩን አውቆ ከመምራት አንጻር መጠነ ሰፊ የሆነ የአቅም ውስንነት ነበረበት:: የሸንኮራ አገዳ ምርት እንዲሰጥ የሚፈልጋቸውን ግብዓቶች በአግባቡ ባለማግኘቱ የአገዳ ምርት እጥረት ነበር:: አርሶ አደሩም በመጎዳቱ ከፋብሪካው ጋር ያለውን ውል እያቆመ ወደ ሌላ ምርት ሄዷል:: ይህም ፋብሪካው በዓመት ከ300 መቶ እስከ 350 ሺህ ኩንታል ብቻ ወደ ማምረት እንዲወርድ አድርጎታል::

እንደ ቦርድ ሰብሳቢው ገለጻ፤ የስኳር ምርት ችግርን በመሠረታዊነት ለመለወጥ ከአርሶ አደሩ ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጓል:: ከማዕቀፉ የወጡ አርሶ አደሮች ወደ ማዕቀፉ እንዲመለሱ ተደርጓል:: ለአገዳ ምርት የሚሆኑ ግብዓቶች ላይ አቅርቦቶች እንዲሻሻሉ ተደርጓል:: በ2017 የታቀደው አንድ ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት ካለፈው ዓመት ጀምሮ ዝግጅት እየተደረገ ነው:: የሸንኮራ ምርት ሽፋንን 14 ሺህ ሄክታር የማድረስ እቅድ የተያዘ ሲሆን አሁን ከ5 ወደ 9 ሺህ ሄክታር መሬት ማደጉንም ጠቅሰዋል::

እንደ ኃላፊዎቹ ገለጻ፤ የስኳር ፋብሪካዎችን ችግር በመለየት መፍሔት መስጠት ያስፈልጋል:: ስኳር ፋብሪካዎች ወደ ምርት እንዲገቡ አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት፣ የውጭ ምንዛሪ ችግርን መቅረፍ፣ በራሳቸው እንዲደራጁ ማድረግና አሠራርን ማዘመን ያስፈልጋል::

እንዲሁም ፋብሪካዎች የራሳቸው የሆነ በቂ የአገዳ ምርት ማምረቻ መሬት እንዲኖራቸው በማድረግ ከውጭ የሚገባውን የስኳር ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት መተካትና ኢትዮጵያ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማድረግ እየተሠራ ነው::

# ግብርና

# ሜካናይዜሽንን በማስፋፋት የአንበሳውን ድርሻ እየተጫወተ ያለው ባንክ

በኃይሉ አበራ

በግብርናው ዘርፍ እየተመዘገበ ያለውን የምርትና ምርታማነት እድገት ለማስቀጠል፣ አርሶ አደሩን ከእጅ ወደ አፍ አመራራት ለማውጣት ሚናቸው ከፍተኛ ከሆነ ቴክኖሎጂዎች መካከል የሜካናይዜሽንን ማስፋፋት አንዱ ነው። ሜካናይዜሽን ማሳን ለዘር በማዘጋጀት፣ በዘር በመሸፈን፣ ሰብሉ ሲደርስም ለማጨድና ለመውቃት፣ በመስኖ እርሻም በውሃ ማሳቢያ መሳሪያዎች ለመገልገልና ለመሳሰሉት ተግባሮች ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለመሆን የዋጋው ውድነት፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም የነበረው የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ደንቀራ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል። መንግሥት እነዚህን መሰል የግብርናው ዘርፍ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ ብዙ መሠራቱን ተከትሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትራክተሮች፣ ኮምባይነሮች፣ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችና የመሳሰሉት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ መሆን ጀምረዋል።

አቅርቦቱም በክልል መንግሥታትና በፌዴራል መንግሥት በኩል ሲፈጸም ይስተዋላል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክም በማሽን ሊዝ ሥርዓት ለአርሶ አደሮችና የሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ ኮምባይነሮችን ትራክተሮችንና የመሳሰሉትን እያቀረበ ይገኛል። ባንኩ በቅርቡም የግብርና ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉት የእነዚህ የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ርክክብ ከሊዝ ደንበኞቹ ጋር አድርጓል።

ባንኩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በተመረጡ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለተሰማሩ የፋይናንስ ደንበኞቹ ግብዓቶችን ሲያቀርብ ቆይቷል። በተለይ በማዕድንና በግብርና ሥራ ለተሰማሩ የሊዝ ደንበኞቹ የሚሰጠው ፋይናንስም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።

ከንግድ ባንክ ቀጥሎ ከፍተኛው ፋይናንስ አቅራቢ እንደሆነ የሚገለጸው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከ40 ቢሊየን ብር በላይ ካፒታል ማፍራት ችሏል። በቅርቡም በቃሊቲ ከሚገኙት ወረታ ኢንተርናሽናልና በሞይንኮ ኢንተርናሽናል እንዲሁም በቢሾፍቱ ከተማ ከሚገኘው ሐግቤስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር ያስመጣቸውን 10 ኮምባይነሮች፣ 15 ትራክተሮች እንዲሁም 14 እስካቫተሮችን በግብርና ዘርፍ እና በማዕድን ልማት ዘርፍ ለተሰማሩ የሊዝ ፋይናንስ ደንበኞቹ አስረክቧል።

በርክክቡ ወቅት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እንዳሉት፤ ባንኩ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ለሊዝ ደንበኞቹ የሚሰጠው የሊዝ ፋይናንስ ድጋፍ ከነበረበት ሁለት ቢሊየን ብር አሁን ወደ 11 ቢሊየን ብር አድጓል።

የሀገሪቱ የእርሻ ሥራ በአነስተኛ ማሳ አርሶ አደሮች ይዞታ ላይ የሚካሄድ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህ ዓይነት ልምምድ ግብርናን ወደ ትልቅ ኢንቨስትመንት ማሳደግም አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል፤ አርሶ አደሮች ትራክተር እና ኮምባይነር ገዝተው መሥራት እንደሚከብዳቸውም አስታውቀዋል።

በሊዝ ፋይናንሲንግ አሰራር /ሞዳሊቲ/ ግን እርሻው የኩታ ገጠም መልክ እንደሚኖረው ጠቅሰው፣ ይሄንን አገልግሎት የሚሰጡ ደንበኞች አርሶ አደሮቹ ዘንድ ሄደው በኪራይ መሬታቸውን እንደሚያርሱላቸው፣ ሰብሉ ሲደርስም እንዲሁ አጭደው፣ ወቅተውና እህሉን ሰብስበው እንደሚያስረክቧቸው አብራርተዋል።

ይህ ዓይነቱ አሰራር የግብርና ሜካናይዜሽንን በቀላሉና በስፋት ወደ ግብርናው እንዲገባ እንደሚያግዝ የባንኩ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አስታውቀዋል፤ ሰብል በመሰብሰብ ወቅት 30 በመቶው ምርት እንደሚባክን ጥናቶች ማመላከታቸውን ጠቅሰው፣ ሜካናይዜሽን በአጨዳ ጊዜ ሊባክን የሚችለውን ምርት ለመጠበቅ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ብለዋል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት እንዳስታወቁት፤ ብቸኛው የፖሊሲ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማትን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ኢንቨስትመንትን በመደገፍ ሰፋፊ ሥራዎችን ይሠራል። ባለፉት አምስት ዓመታት ሰፊ የሪፎርም ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህ የማሻሻያ ሥራውም በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ፈትቶ ዛሬ በኢትዮጵያ ካሉ ባንኮች በካፒታል ደረጃ ሁለተኛው ከፍተኛ የካፒታል ደረጃ ላይ ደርሷል። በአሁኑ ወቅትም ባንኩ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመቀጠል ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። እስከ 40 ቢሊየን ብር የሚደርስ ካፒታል ያለው ሲሆን፣ በዚህም በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በተመረጡ የአገልግሎት ዘርፎች የሚደረጉ ልማቶችን በመደገፍ በኩል ከፍተኛ ሥራ እየሰራ ይገኛል።


ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

ባንኩ 10 ኮምባይነሮችን እና 15 ትራክተሮችን ስሲዝ ደንበኞቹ አስረክቧል

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በግብርናው ዘርፍ በሁለት መልኩ ድጋፍ እያደረገ ሲሆን፤ አንደኛው በሊዝ ፋይናንሲንግ፣ ሁለተኛው ደግሞ በፕሮጀክት ፋይናንሲንግ የሚሰጠው ድጋፍ ናቸው። የሊዝ ፋይናንሲንግ ልዩ ሲሆን፣ ልዩ የሚያደርገውም ደንበኞች ለሥራ ማስኬጃ የሚያገለግለውን 20 በመቶ እንዲያዘጋጁ ተደርገው ቀሪውን 80 በመቶ ባንኩ በራሱ በሚያደርገው ፋይናንስ ማሽነሪዎችን አስመጥቶ በሊዝ መልክ በማቅረቡ ነው። በተለይ ከተለያዩ ተቋማት ተመርቀው ለሚወጡ ወጣቶች ቀላልና ቀልጣፋ አሰራር በመከተል ብዙ የካፒታል ንብረት ሀብት ለሌላቸው ግለሰቦች ማሽነሪው እንደማሰያዣ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገቡ ያደርጋል።

የሀርቨስተር ኮምባይነር ርክክብ ሲደረግ ያገኘናቸው አቶ መሀመደ ሀጂ ከድር ከኦሮሚያ ክልል አርሲ ቦቆጂ የመጡ የአርሶ አደር ልጅ ናቸው። እሳቸው የወላጅ አባታቸው በባህላዊ መንገድ አዝመራውን ሲያጭዱ ከፍተኛ የሆነ የምርት ብክነት ሲከሰት አስተውለዋል። በዝናብ ወቅት ለመሰብሰብም ከባድ መሆኑን ተረድተዋል። ልማት ባንክ እነዚህን ማሽኖች በሊዝ ማቅረቡ ምርትን በጊዜ ለመሰብሰብ እና ብክነትን ለመቀነስ ትልቅ እገዛ በማድረግ የአርሶ አደሮችን ችግር ያቃልላል፤ ሀገርንም ያሳድጋል ብለዋል።

‹‹አባቶቻችን ምርት ሲሰበስቡ ይቸገሩ የነበረበት ሁኔታ በእጅጉ ይሰማኝ ነበር›› ያሉት አቶ መሀመድ፣ እሳቸው በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ ወደሚታገዘው የግብርና ሥራ መግባት መቻላቸውን ነው የገለጹት። ወደፊትም ከልማት ባንክ ጋር በመሥራት በኢንዱስትሪው ዘርፍም መሰማራት እንደሚፈልጉ አስታውቀዋል።

ልማት ባንክ ማሽነሪዎቹን በወቅቱ ማቅረብ እንዳለበት አስገንዝበው፣ ማሽኖቹ አሁን የመጡት አጨዳው እያለቀ ባለበት ወቅት እንደሆነም አመላክተዋል። እሳቸው በሊዝ ደንበኝነት ማሽኑን ለመግዛት አስፈላጊውን ቅደመ ሁኔታ አሟልተው ሁለት ዓመታት ያህል መጠበቃቸውን አስታወሰው፣ ልማት ባንክ ብቻ ሳይሆን ከልማት ባንክ ጋር የሚሰሩ ድርጅቶችም በመናበብ ማሽኖቹ ወደብ ላይ የሚኖራቸውን ቆይታ ማሳጠር እንደሚገባቸው ጠቁመዋል። ማሽኑ የጭነት መኪና እንደሚፈለግ አቶ መሀመድ አስታውቀው፣ ለእዚህም 200 ሺህ ብር ያህል እንደሚጠየቅ ገልጸዋል። ይህም ከሊዝ ፋይናንሲንግ ጋር ቢታይ ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል።

ሌላው ትራክተር የተረከቡት የአዲናስ እርሻ ልማት ባለቤት አቶ በሪሁን አበራ በበኩላቸው ወደ እርሻ ሥራ ከመግባታቸው በፊት በእንቁላል ንግድ ተሰማርተው ሰርተዋል፤ በእዚህም ከጎጃም ወለጋ፣ ደምቢዶሎ፣ አሶሳ መንዲ ድረስ በበቅሎ እየተጓዙ ነግደዋል። ከዚህ በኋላ ነው ወደ እርሻ ሥራው የገቡት። ሌሎች ትራክተሮችም እንዳላቸው የሚናገሩት አቶ በሪሁን፣ ትራክተሩን ከልማት ባንክ በሊዝ መግዛት በመቻላቸው ተደስተዋል።

አቶ በሪሁን ቀደም ሲል ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ላይ እርሻ እንደነበራቸውና በፀጥታ ችግር ሳቢያ እንዳቆሙ አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ምስራቅ ጎጃም እና አዊ ዞን ላይ በ400 መቶ እና በ500 ሄክታር የእርሻ መሬት ላይ የግብርና ሥራቸውን እንደሚያከናወኑ ተናግረዋል።

የእርሻ ሥራ በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው በልምድ ላይ ተመስርቶ መሆኑን አቶ በሪሁን ጠቅሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት ድጋፍ ትራክተሮች በብዛት ወደ ሥራ እየገቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የአርሲ ዞኑ ሄጦሳ ወረዳው አቶ ፈይሳ ጉታም ትራክተር እና ሀርቨስት ኮምባይነር ተረክበዋል። አርሶ አደሩ ከአንድ ጥማድ በሬ በመነሳት ወደ እርሻ ሥራው የገቡ ናቸው። አሁን ግን ወደ ሜካናይዜሽን ደረጃ ከፍ ማለት ችለዋል። ከልማት ባንክ ትራክተር እና ኮምባይነር መረከባቸውን ጠቅሰው፣ ልማት ባንክ አርሶ አደርን ማዕከል በማድረግ ግብርናውን ወደ ዘመናዊ የእርሻ ሥራ እያሻገረ መሆኑን አስታወቀው፣ ለዚህም አመስግነዋል። ወደፊትም ባንኩ ከአርሶ አደሩ ጎን መሆን ከቻለ የተሻለ መሥራት እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ከ15 ዓመታት ልፋትና ድካም በኋላ ዛሬ ላይ በተሻለ የግብርና ቀመና ላይ መድረስ እንደቻሉ የገለጹት አቶ ፈይሳ፤ በእርሻ ሥራ ላይ ወስኖ መግባት ከተቻለ መለወጥ እንደሚቻል ጠቁመዋል። አሁን በክላስተር በመሆን ስንዴ እያለሙ መሆናቸውን ገልጸው፣ ግብርናውን ወደ ሜካናይዜሽን በመቀየር በኩል ልማት ባንክ የአንበሳውን ድርሻ እየተጫወተ ነው ብለዋል።

ከሀገሪቱ ሕዝብ አብዛኛው አርሶ አደርና አርብቶ አደር ለሆነባት ሀገር ትራክተሮችና ኮምባይነሮች ለአርሶ አደሮች መቅረባቸው ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው ሽግግር ከፍተኛ ሚና እንዳለው አስታውቀዋል። ብቻህን በበሬ በማረስ ብቻ ወደሚፈለገው ግብ መድረስ አይቻልም ያሉት አቶ ፈይሳ፣ ሜካናይዜሽኑ ሥራችንን የበለጠ በማሳለጥ ወደ ውጤታማነት ያደርስልናል ብለዋል።

አርሶ አደሩ ትናንት ከእጅ ወደ አፍ የነበረው የእርሻ ሥራቸው ከራሳቸው ተርፎ ለገበያ እየወጣ መሆኑን ጠቁመዋል። ‹‹ቀስ ብሎ በመሄድና በሩጫ በመሄድ መካከል ልዩነት እንዳለ ሁሉ በበሬ በማረስ እና በትራክተር አርሶ በሀርቨስት ኮምባይነር መሰብሰብ የጎላ ልዩነት አለው›› ብለዋል።

በሜካናይዜሽን ስንጠቀም ሀገራችን ራሷን በምግብ ለመቻል ከምታደርገው ጥረት አልፎ ለውጭ ገበያ ለማቅረብም ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክተው፤ ‹‹እኔ ለራሴ ብዬ ሳመርት ለገበያም ጭምር በመሆኑ በተዘዋዋሪ ለሀገር እድገት የጎላ ሚና አበረክታለሁ ብለዋል።

የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን የተከናወኑ ተግባሮችን ተከትሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘር እና በአዝመራ መሰብሰብ ወቅት ትራክተሮችና የአዝመራ መሰብሰቢያ ኮምባይነሮችን በስፋት ማየት ተለምዷል። ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችም እየተበራከቱ ይገኛሉ። የክልል መንግሥታት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትራክተሮችንና ኮምባይነሮችን እና ለመስኖ ልማት የሚውሉ የውሃ ማሳቢያ ሞተሮችን ለአርሶ አደሮች እያቀረቡ ይገኛሉ።

የአርሶ አደሮች የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ፍላገት እየጨመረ ቢመጣም፣ አርሶ አደሮች በጠየቁት ልክና በጠየቁበት ወቅት ማሽነሪዎቹን ማግኘት እንዳልቻሉ እየጠቆሙ ይገኛሉ። ይህን የአርሶ አደሩን ጥያቄ መመለስ ላይ አሁንም በትኩረት መሥራት ይገባል። አርሶ አደሩ የሜካናይዜሽን ፍላጎት እንዲኖረው ተደርጎ አቅርቦት ላይ ፈጣን አለመሆን በግብርናው ዘርፍ የሚፈለገው ደረጃ ላይ ለመድረስ በተያዘው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል።

በመሆኑም ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን የሚያቀርቡ ተቋማት፣ ክልሎች፣ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በዚህ ላይ እያከናወኑ ያሉት ተግባር ሊበረታታ የሚገባው ሆኖ፣ እየተፈጠረ ያለውን የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# መልካም ድባብ የፈጠረው የዩኒቨርሲቲዎች አቀባበል

ግርማ መንግሥቴ

ከአንዳንድ ጉዳዮች አኳያ ካየነው ሳምንቱም ሆነ ወሩ፤ ወይም እያንዳንዱ ወቅት፣ አንዱ ከአንዱ ጋር እኩል አይደለም። ወይም፣ አቻነት አይስተዋልበትም። በመሆኑም በዓመቱ ውስጥ ያሉት 52 ሳምንታት መንትያ ናቸው ማለት አይቻልም። ይበላለጣሉ፣ ይለያያሉም። ልዩነታቸው ደግሞ እንደ ነጮቹ በቀን ብዛትና ማነስ ሳይሆን በሚያስተናግዷቸው ሀገራዊ ሁነቶች ነው።

ያለፉት ሳምንታት፣ በተለይም ያለፈው ሳምንት በከፍተኛ ትምህርት (ዩኒቨርሲቲዎች) አካባቢ ደምቆና አሸብርቆ ነው ያለፈው። ምናልባትም ቀደም ባሉት ጊዜያት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተመረቀ ሰው ጉዳዩ ያኔ የሌለና እንግዳ ነገር በሚመስል መልኩ ሳምንቱ በየተቋማቱ ልዩ ነበር። ይህ “መቼ ተጀመረ፣ እንዴት ተጀመረ፣ ለምን ተጀመረ?” የሚሉ ጥያቄዎችን እስካላስነሳ ድረስ የሁነቱ ዕድሜ ቅርብ መሆኑን መግለፅና በሳምንቱ ውስጥ የነበረውን ገፅታ አስመልክቶ የተወሰኑ ሃሳቦችን ማንሳት ይቻላል።

ምንም እንኳን ነባሩና ዘመናትን ያስቆጠረው የትምህርት ቤቶች የመከፈቻ ጊዜ (ወር) መስከረም ቢሆንም እራሳችን ባመጣነው ጣጣ ይህ በመስከረም የመከፈትና በሰኔ የመዝጋቱ ጉዳይ ተግዳሮት እየገጠመው ከመጣ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡በመሆኑም፣ ዛሬ ዛሬ የትምህርት ቤቶች የመከፈቻም ሆነ መዝጊያ ሰሞን ከ“አንፃራዊ ሰላም” ጋር እየተያያዘ መሆኑና “አንፃራዊ” የተባለው ሰላምም እየራቀ በመምጣቱ የመከፈቻና መዝጊያ ወቅቶች እንደየአካባቢውና እንደ ተቋሙ ወቅታዊ ይዞታ እየተለያየ መጥቷል።

መለያየት ብቻም አይደለም፤ አንዳንድ አካባቢዎች መከፈቱም ሆነ መዝጋቱ ከናካቴው እየተረሳ የመጣ ይመስል የትምህርት ተቋማት ሥራ አቁመው ተማሪዎች በመባከን ላይ ይገኛሉ። ለዚህ ደግሞ ሰሞኑን በአማራ ክልል በሚገኙ 10 ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች በማህበራዊ ድረገፆች (በተለይም በቴሌግራም) “ያለ ትምህርት ቁጭ ብለን ወራት አልፈዋል፤ ፍትህ እንሻለን” ከሚለው በላይ መረጃም ሆነ ማስረጃ የለም።

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ድሮ በማያወላውል መልኩ “መስከረም” መክፈቻ ሲሆን፣ “ሰኔ” መዝጊያ ነው። ዛሬ ይሄ አለ? የለም። ባለመኖሩ ምክንያትም የትምህርት ተቋማት የመክፈቻና የመዝጊያ (የማስመረቂያም ጭምር) ወቅቶች (ወራት) ዓመቱን ሙሉ ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ ሲከናወኑ ይታያል። ለአንዱ የመዝጊያ ወቅት የሆነው ለሌላው የመክፈቻ ይሆንና ግራ እስኪያገባን ድረስ ግር ይለናል።

ይህ የመክፈቻና የመዝጊያ መዘበራረቅ (በክረምቱ መርሀ-ግብር ሳይቀር) በመክፈትና መዝጋት ብቻ የሚቆም እንዳልሆነ ይታወቃል። ወደ ክፍል ውስጥ መማር-ማስተማሩ ሁሉ ይገባና “ክራሽ ፕሮግራም”፣ “ሰፕሊመንታሪ”... የሚሉ፤ ድሮ ብዙም የማይታወቁ የግር ግር መማር-ማስተማር ተግባራት እንዲካሄዱ አድርጓል። ተማሪው ስለ “ሀ” ሳይረዳ “ፐ” ላይ የሚያደርሱት እነዚህ ፕሮግራሞች ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለትምህርት ጥራት ውድቀት የራሳቸውን አስተዋፅኦ አላበረከቱም ማለት ስለማይቻል ወደ ድሮው የመክፈቻና መዝጊያ ሥርዓት ይመለሱና ሁሉም ነገር በተረጋጋ መልኩ ይከናወን ዘንድ የሚመለከተው ሊረባረብ ይገባል፡፡

የባለፈው ሳምንት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድምቀትና አሸብርቆት እንመለስ። ከሀዋሳም እንጀምር። የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳሙኤል ጂሎ እንደሚገልፁት፣ ዩኒቨርሲቲው 4 ሺ የተፈጥሮ ሳይንስ እና 2 ሺ የማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪዎችን በድምሩ 6 ሺ ተማሪዎችን ተቀብሎ ወደ መማር-ማስተማር ተግባሩ ገብቷል።

ሌሎቹስ? አሁን፣ ለ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የማለፊያ (መቁረጫ) ነጥብ በማምጣት በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡለትን 832 አዲስ ገቢ ተማሪዎች ተቀብሎ የመዘገበውን አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ጠቅሰን፤ በሀገሪቱ ከሚገኙ 15 የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ የሆነው ዲላ ዩኒቨርሲቲም በተመሳሳይ ምዝገባና ቅበላን አጠናቅቆ ወደ ተግባር መግባቱን አመልክተን፤ አስፈላጊዎቹን የመመገቢያ፣ የማስተማሪያ እና የመኝታ አገልግሎቶች በማሟላት ለዚሁ ዓመት (የትምህርት ዘመን)



የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሰሞኑን አቀባበል ያደረገላቸው አዳዲስ ተማሪዎች በከፊል፣

> **በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ድሮ በማያወላውል መልኩ “መስከረም” መክፈቻ ሲሆን፣ “ሰኔ” መዝጊያ ነው። ዛሬ ይሄ አለ? የለም**

የተመደቡለትን 364 የተፈጥሮ እና የማህበራዊ ሳይንስ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ተቀብሎ የማስተማር ሥራውን መጀመሩን የራያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ታደሰ ደጀኔ መግለፃቸውን አንስተን ወደ መደወላቡ እንሂድ።

በ2016 ዓ.ም በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ አዲስ የተመደቡ፤ እንዲሁም፣ በ2015 ዓ.ም የሪሜዲያል ፕሮግራም የተከታተሉና የማለፊያ ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች ምዝገባ ታኅሣሥ 15 እና 16/2016 ዓ.ም መሆኑን ያስታወቀው መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማሩ ተግባርም ታኅሣሥ 17/2016 ዓ.ም እንደሚጀምር አስታውቋል። ጅግጅጋስ?

“ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የ2016 ዓ.ም የድህረ-ምረቃ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች (በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጠውን የድህረ-ምረቃ የመግቢያ ፈተና (GAT) ወስደው ያለፉ አመልካቾች) ምዝገባ ከታኅሣሥ 05 እስከ 11/2016 ዓ.ም” ያካሄደና ወደ ሥራ የገባ መሆኑም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው የዚሁ ወር የአዲስ ገቢ ተማሪዎች ቅበላና ምዝገባ ክንውን አካል ነው። ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንምጣ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2016 የትምህርት ዘመን በመደበኛ መርሐ ግብር የመጀመሪያ ዲግሪ አዲስ የተመደቡ ተማሪዎች የማመልከቻ እና ወደ ዩኒቨርሲቲ ሪፖርት ማድረጊያ ጊዜውን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ይፋ በማድረግ ቅበላውን ታኅሣሥ 09፣ 10 እና 11/2016 ዓ.ም በደመቀና ባሸበረቀ ሁኔታ ሲያካሂድ ቆይቷል። የምዝገባው ፕሮግራም በተለያዩ ዝግጅቶች የታጀበ ሲሆን፣ ከሚኒ ሙዚቃ ባንድ ጀምሮ የተለያዩ ድርጅቶችና ስፖንሰር አድራጊዎች ተገኝተው ለፕሮግራሙ ድምቀትን አጋርተዋል።

እንደ ሌሎቹ ተቋማት ሁሉ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቅበላ ዝግጅት ታስቦበትና ታቅዶ ስለመሆኑ ከዋናው ካምፓስ መግቢያ በር ጀምሮ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የሚገልፁ ሲሆን፣ ከፌዴራል ፖሊስ ጀምሮ ያሉት የፀጥታ ኃይላት፣ ተማሪዎቹን መረጃዎቻቸውን እየተመለከቱ የሚያረጋግጡ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች፣ ልዩ መለያን የለበሱና ልጆቹን (ሻንጣቸውን ተቀብሎ እስከ ማገዝ ጭምር) ይዞ ወደ ውስጥ የሚያስገቡና የሚያስተናግዱ የፈቃደኞች (ቮለንቲየርስ) ቡድን አባላት፣ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ባንኮች ጊዜያዊ ቢሮዎች፣ ነፃ ለስላሳ መጠጥ አቅራቢዎች፣ እዚህም እዛም የተሰቀሉና የተለጠፉ የ“እንኳን ደህና መጣችሁ” መልእክቶች ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።

በዚሁ ምክንያትም የአዲስ ገቢ ተማሪዎች ፊት በደስታ ፈክቶ የሚታይ ሲሆን፣ አንድም የእንግድነትና ባይተዋርነት ስሜት ሲንፀባረቅባቸው አልተስተዋለም። በግቢው ውስጥ ተዘዋውረን እንደተመለከትነውም አዲስ ገቢዎቹ ከነባሮቹ ጋር በእኩል የመንፈስና የስሜት ደረጃ ላይ ሆነው ነው ያገኘናቸው። እዚህም እዛም ባሉት መዝናኛ ክበባት ውስጥ ሻይ/ቡና ሲባባሉ፤ በየጥላዎቹ ስርና ሣር ላይ ጋደም እያሉ ሲጫወቱ ነው ያየናቸው።

በቡድን በቡድን ወደተቀመጡት በማጋደል ከውጭ ወደ ውስጥ ሲገባ በስተ ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት በኩል ሶስት ሆነው፣ ጋደም ብለው ከሚጨዋወቱት ጋ ጠጋ አልን። ከሰላምታና የማንነት መረጃ ልውውጥ በኋላም በቀጥታ ወደ ጉዳያችን ገባን።

ባነጋገርኳቸው ቅደም ተከተል ሲቀመጡ፤ ሰጠኝ ደፋሩ፣ ደመረ መንግሥቱ እና ዮሐንስ ሽታ ይባላሉ። ሶስቱም የአንድ አካባቢ ልጆች ናቸው (ሰሜን ሸዋ፣ መራቤቴ)፣ ሶስቱም አንድ ትምህርት ቤት (ፌጥራ) ነው የተማሩት፤ አሁን ደግሞ ሶስቱም አንድ ዩኒቨርሲቲ፣ አንድ ካምፓስ ደርሷቸው ዘና፣ አረፍ ባለ መልኩ፣ ለምለሙ ሳር ላይ ጋደም ብለው የሆድ የሆዳቸውን ይጨዋወታሉ።

ለሶስቱም ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ነበር ያቀረብኩላቸው። የመጀመሪያው “ምን ተሰማችሁ?” የሚል ሲሆን፣ የሶስቱም መልስ “ደስታ” የሚል ነበር።

“አቀባበሉን እንዴት አገኛችሁት” ለሚለውም፣ “ያልጠበቅነው ነው። በርግጥ በፊትም ቢሆን ችግር ይገጥመናል ብለን አላሰብንም። ግን ደግሞ በዚህ መልኩ ይቀበሉናል ብለንም አላሰብንም። በመሆኑም፣ አቀባበላቸው ትንሽ ለየት ብሎብናል፤ ያስደስታል።” በማለት ነው የመለሱት።

“ቤተሰቦቻችሁ እንዴት ሆነው ይሆን፣ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ሌሎች የሚያውቋችሁም ሆኑ ወዳጅ ዘመዶቻችሁ ሊጨነቁ ይችላሉ። ለእነሱ ምን የምትሏቸው ነገር አለ?” ለሚለው ድንበር ተሻጋሪ ጥያቄያችንም “በደህና ደርሰናል። ምግብም ጀምረናል። መኝታ ክፍልም ተሰጥቶናል። ሁሉም ተደርጎልናል። የቀረን ትምህርታችንን በትጋት መከታተል ብቻ ነው። በመሆኑም፣ ምንም የሚያሳስባችሁ ነገር የለም እንላቸዋለን።” የሚለውና ሶስቱም የተስማሙበት፤ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ያስተላለፉት መልእክት ነው።

ምድቡ አምስት ኪሎ (ቴክኖሎጂ ፋክልቲ) የሆነው የአዲስ አበባው የአብፀጋ ደሳለኝም ከእነ ሰጠኝ፣ ደመረ እና ዮሐንስ የተለየ የነገረን ነገር የለም፡፡ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ማለፉ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ውጤት ላመጡ 1 ሺ ተማሪዎች “በምርጫቸው” በሚል በወሰነው መሠረት እዚህ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመመደቡ ደስተኛ መሆኑን አጫውቶናል። ከዚህ ከአብፀጋ ስኬት መረዳት የሚቻለው ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ጥቅሙ ማለፍ ብቻ ሳይሆን የልዩ ዕድል ተጠቃሚነትንም ያመጣልና የወደፊት ተፈታኞች ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል እንላለን።

“በየትኛው የትምህርት መስክ፣ ማለትም የትኛውን የጥናት መስክ ነው መከታተል የምትፈልጉት፤ ፍላጎትና ዝንባሌያችሁ የትኛው ዘርፍ ነው?” ለሚለው ጥያቄያችንም ሰጠኝና ደፋሩ ኢኮኖሚክስ ማጥናት እንደሚፈልጉ የነገሩን ሲሆን፤ የዮሐንስ ምርጫ ግን ሕግ ነው፡፡ “አሁን በትምህርት ላይ ላሉት፣ ለታናናሾቻችሁ ምን መልእክት ታስተላልፋላችሁ?” ላልናቸውም፤ መልሳቸው “በርትተው መማር፣ ጥሩ ውጤት በማምጣት ዩኒቨርሲቲ መግባት አለባቸው።” የሚል ነው።

በደቡብ ሱዳን፣ ጁባ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በ2023/2024 የትምህርት ዘመን በኢትዮጵያ በሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የነፃ ትምህርት ዕድሉን ላገኙና ተጠቃሚ ለሆኑ 120 ተማሪዎች የሽኝት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ የነበረ መሆኑ፤ ነፃ የትምህርት ዕድሉ በሁለቱ ሀገራት መካከል በአቅም ግንባታ እና በሰው ኃይል ልማት ዘርፍ ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚያግዝ፤ እንዲሁም፣ ለተጨማሪ 120 ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ መሰጠቱን በደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ባለሥልጣን አምባሳደር ነቢል ማህዲ አማካኝነት ከኤምባሲው የተገኘ መረጃ አመልክቷል።

እነዚህ ተማሪዎች ባሳለፍነው ሳምንት በሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ደመቅና ሸብረቅ ብለው ያለፉት የቅበላ ፕሮግራሞች አካል መሆናቸውን እዚህ ጋ ጠቅሶ ማለፍ ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተን በነበረበት ወቅት የተመለከትነውም ይህንኑና የነፃ ትምህርት ዕድሉ ተጠቃሚዎች በቡድን በቡድን ሆነው በጊቢው ውስጥ ሲንሸራሸሩ ነው። ለተጨማሪ 120 ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ መሰጠቱን ከኤምባሲው የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

ይህ እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውጭ በሆኑት እና እራሳቸውን ችለው በሚንቀሳቀሱ ተቋማትም እየታየ ያለ ጉዳይ ሲሆን፣ ለዚህ ደግሞ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ተገቢ ማሳያዎች ናቸው። ኅዳር 5 ቀን 2016 ዓ.ም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ላምበረት በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው ሰልጣኞችን በመቀበል ላይ ናቸው።

መግለጫውን የሰጡት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል እንዳሉት ከሆነ “በ2016 ዓ.ም 844 ሺህ 384 የሚሆኑ ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ወስደዋል። ከእነዚህ ውስጥ በእኛ ምልከታ 632 ሺህ 587 የሚሆኑት ወደ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ይመጣሉ የሚል ግምት አለን” ያሉ ሲሆን፣ “የሰው ኃይል ለመቀበል የተሻለ ዝግጁነት አላቸው ያልናቸውን የመንግሥትና የግል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን ፈትሸናል ያሉት ሚኒስትሯ፣ እስካሁን ባለው ከ28 ሺህ በላይ የሚሆኑ አሰልጣኞች፣ ወደ 1ሺህ 400 ገደማ የተሻለ ብቃት ያላቸው ማሰልጠኛ ኮሌጆች” እንዳሉም አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ በዓመት 600 ሺህ ተማሪዎችን ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የመቀበል አቅም መፈጠሩን ከዚህ በፊት ሚኒስቴሩ ማስታወቁም ይታወሳል።

በጥቅሉ ያለፈው ሳምንት በአብዛኞቹ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ለ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የማለፊያ (መቁረጫ) ነጥብ በማምጣት በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡላቸውን አዲስ ገቢ ተማሪዎች በልዩ ሥነ ሥርዓት የተቀበሉበት፣ አዲስ ገቢ ተማሪዎቹም በልዩ መስተንግዶና አቀባበሉ የተደሰቱበትና በቀናት ውስጥ የነባር ተማሪነትን መንፈስ የተላበሱበት ወቅት ሆኖ አልፏል።

ይህን የአቀባበል ጉዳይ እንደ ማሳያ አድርገን ወስደን እዚህ ጠቀስነው እንጂ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች አቀባበል ተደርጎ ሁሉም ገብተዋል ማለታችን አይደለም። ያልገቡ አሉ። የገቡት የተደረገላቸውን አቀባበልና ያገኙትን የመንፈስ እርካታ ያልገቡትም እንደሚያገኙት ይጠበቃል።

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ በድርድሩ ላይ የአካሄድ ለውጥ ማድረግ ይጠበቅባታል››

- አቶ ግርማ ባልቻ- ዲፕሎማትና ደራሲ

እፀገነት አክሊሉ

**አቶ ግርማ ባልቻ በግብ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ለስድስት ዓመታት በዲፕሎማትነት አገልግለዋል። ከዚያ በፊትም በዜግነትና የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤት ውስጥ በተለያዩ የሥራ መደቦች ለሀገራቸውን ግልጋሎት ሰጥተዋል። እኚህ ዲፕሎማት ከግብጽ ተልዕኳቸው መልስ “ናይልና እና የግብጽ ኢኮኖሚያዊ ይዞታ ከትናንት እስከ ዛሬ” የሚል መጽሐፍ አሳትመው ለንባብ አብቅተዋል። አዲስ ዘመን ጋዜጣ በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል በሕዳሴው ግድብ ዙሪያ እየተካሄዱ ያሉትን ድርድሮችና በተለይም 4ኛው ዙር ውይይት ያለ ውጤት መጠናቀቅን አስመልክቶ ቃለ ምልልስ አድርጎ እንዲህ አቅርቧል።**



**አዲስ ዘመን፡- በሕዳሴ ግድብ ድርድር ወቅት በግብፆች በተደጋጋሚ ከሚነሱ የመከራከሪያ ጥያቄዎች ውስጥ ታሪካዊ የውሃ መብት የሚለው ይነሳል፡፡ ለመሆኑ ግብፆች ታሪካዊ መብት የሚሉት ምን ማለት ነው?**

**አቶ ግርማ ፡-** ግብጾች በዓባይ ወይም በናይል ላይ አለን የሚሉት ታሪካዊ መብት እንግዲህ ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ በተለይም ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ጀምሮ ናይልን አስመልክቶ ያወጧቸው ሕጎች ናቸው። ለምሳሌ 1929ኙ ስምምነት የሚባል አለ፡፡ ይህ ስምምነት በውሃ አጠቃቀሙ ላይ ሙሉ መብቱን የሚሰጠው ለግብጾች ነው። በመሆኑም እነዚህን ሕገ ወጥ የሆኑ የተፋሰሱን ሀገሮች በሙሉ ያላሳተፈ በተለይም ኢትዮጵያ ደግሞ የሁነቱ አካል ያልሆነችበት ስምምነትን መነሻ በማድረግ ነው እንግዲህ ታሪካዊ ባለመብት ነን የሚሉ ሃሳቦችን እያራመዱ ያሉት።

ከዚህ በመነሳትም ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ውሃው ላይ ሙሉ ባለመብት ነን የሚል የኮሎኒያሊስት አስተሳሰብ ሲያራምዱ ቆይተዋል። ለዘመናት ይህንን ሃሳብ ይዘው ወደ ክርክርና ድርድር አውድ ይውጡ እንጂ ዓለም አቀፉ ሕግም ግን የሚቀበለው አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- በ1929 እና በ1959 በተፈረሙት ውሎች ላይ ኢትዮጵያ የነበራት ሚና ምንድን ነበር? እንዴትስ ይገለጻል?**

**አቶ ግርማ ፡-** ይህ ስምምነት አንደኛ ደረጃ ሁለት ወገኖች ያደረጉት ነው፡፡ ሁሉም ባለመብቶችም ተካተውበታል ማለት አይቻልም፡፡ ኢትዮጵያን ያላሳተፈ ውል ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ መብት ሊኖረው አይችልም፡፡ ኢትዮጵያም የምትከተለውን ክርክር አሳማኝ የሚያደርገው አንዱ ቅድመ ሁኔታም ይህ ነው።

በወቅቱ እንግሊዞች በቅኝ ግዛት የያዙት ግብጾችን ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ ራሷን በራሷ የምታስተዳድር በማንም ቅኝ ግዛት ውስጥ ያልነበረች ነፃ ሀገር ነበረችና ስምምነቱ እሷን አይመለከትም ነበር። በሌላ በኩልም የ1959ኙ ስምምነት በግብጽና በሱዳን መካከል የተደረገ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ነው የማይመለከታት መሆኑን ያሳወቀችው።

በእነዚህ ምክንያቶች ሁለቱም ስምምነቶች ኢትዮጵያን ሊገዙ የማይችሉ እና ስምምነቱንም ልታከብር የማትገደድ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል። በመሆኑም ሕጎቹ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው እንደውም ሕገ ወጥነታቸው ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት የውሃውን ዋነኛ ምንጭ ሀገር አግልሎ መስማማት ዘለቄታዊ ያልሆነ ከመሆኑም በላይ ሕጋዊነትም ስለሌለው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ በግብጽ በኩል እነዚህ ወሎችና ስምምነቶች በመከራከርያነት የሚነሱት ድርድሩን ለማደናቀፍ ነው ብሎ ማለት ይቻላል?**

**አቶ ግርማ ፡-** እኔ የሕዳሴውን ግድብ ድርድር የማየው አጀንዳ መቀየሪያ አድርጌ ነው። ይህ ድርድር የመጣው 2010 የተፈረመው ሁሉን አቀፍ ስምምነት (የተፋሰሱ ሀገሮች) የሚተዳደሩበት ነው። ይህ መድረክ ግብጾች የተሸነፉበት ሲሆን በወቅቱም ሱዳንና ግብጽ ከስምምነት ማዕቀፉ ወጡ። ሌሎቹ በግላቸው ስምምነት ላይ ደረሱ፡፡ አሁን ደግሞ በተደጋጋሚ የሚያደርጉት ነገር ይህንን ተሸንፈው የወጡበትን ስምምነት ለማፍረስ እና አጀንዳ ለማስቀየር የሚያደርጉት ጥረት እንጂ የግድቡ ግንባታ ይህንን ያህል ትልቅ አጀንዳቸው ሆኖ አይደለም።

መጀመሪያ ሲጀምሩትም ውሸታቸውን ነበር፤ ነገር ግን በተለይም እኛን በዚህ መልኩ አታካች በሆነ የድርድር ሂደት ውስጥ አስገብተውንና አስረውን ከቻሉም ደግሞ ሃሳባችንን አስቀይረው ወደመስመራቸው በማስገባት ሊያስፈርሙን ነበር ፤ በጠቅላላው ግን ስምምነቱ ዝም ብሎ ጊዜ መግዢያ ነው። በመሆኑም ከተጀመረ ጀምሮ ስኬት የማይታይበት በጣም እያዘገመ ያለው ያን ያህል ውስብስ ነገር ስላለው ሳይሆን አጀንዳው ሌላ ስለሆነ ነው።

በጠቅላላው ግን ድርድር ድርድር እየተባለ የሚደከመው ነገር በግብጾች በኩል ጊዜ መግዢያ እንጂ ሌላ ውጤት የሚያመጣ ካለመሆኑም በላይ በተለይም እኛን ከመሠረታዊ ነገር አውጥቶን ቅርንጫፍ ላይ እንድናተኩር ለማድረግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተያዘች ብሎም እነሱ የሚያነሷቸው ስምምነቶች ላይ እጇን ያላስገባች ከመሆኑ አንጻር ይህንን ውል የመቀበል ግዴታ አለባት?**

**አቶ ግርማ ፡-** በፍጹም ይህንን ለማስገደድ የሚችሉበት ምንም ዓይነት የሕግ መሠረት የላቸውም። የሕግ መሠረት ስለሌላቸውም እንዲሁ በድርድሮች ወቅት በማንሳት ላለመስማማት ምክንያት ያደርጉታል እንጂ አንድም ቀን ፍርድ ቤት ይዘነው እንሂድ ብለው አያውቁም።

ብዙ ጊዜ ሀገሮች መሰል ችግሮች ሲገጥሟቸው ወደዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ነው የሚሄዱት እነሱ ግን ያንን መንገድ ሲከተሉ አናይም። ይህ የሚያመለክተው ጉዳዩ ምንም ዓይነት የሕግ መሠረት እንደሌለው ነው፤ ልቦናቸውም ጠንቅቆ ያውቀዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ መሰሉ አካሄድ አሁን ባለው ሁኔታ ለግብጾች ያዋጣል ብለው ይላሉ?**

**አቶ ግርማ ፡-** እውነቱን ለመናገር ምንም የሚያዋጣቸው ነገር የለውም። እንደውም ተጎጂ ነው የሚሆኑት፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያ በተሳካ ሁኔታ የግድቡን ግንባታ ወደማጠናቀቁ ደረጃ ተቃርባለች። በተፋሰሱ ውስጥም እንደዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ተሰርቶ አልቆ አያውቅም። በመሆኑም ፕሮጀክቱ ለሌሎች ሀገሮችም ዓይን ገላጭ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሌሎች ግድቦችንም የመገንባት አቅም እንዳለን ከማሳየታችንም በላይ ሌሎች ሀገሮችም ልክ እንደ ኢትዮጵያ መሥራት ይቻላል ለካ ብለው ሞራል እንዲሰማቸው አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- በፈረንጆቹ 2015 ኢትዮጵያ፣ ግብጽ እና ሱዳን የተፈራረሙት የመርህ ስምምነት ምንድን ነው፤ ይህ ስምምነትን ለመተግባር ግብጾች አሻፈረኝ ያሉት ለምንድን ነው?**

**አቶ ግርማ ፡-** የመርህ ስምምነቱ አንዱ ኢትዮጵያን የመጥለፊያ ሴራ ነበር። ሲጀመር የነበረው ዓላማ ኢትዮጵያን ስህተት ውስጥ ከቶ ውል በማስፈረም የራሳቸውን ተጠቃሚነት ለማስጠበቅ ያሳዩት ፍላጎት ነው። በፊትም እኔ እዛ ሀገር ዲፕሎማት ሆኜ በሰራሁበት ወቅት ሳስተውል ኢትዮጵያ አንድም ፊርማ ፈርማልን አታውቅም ይሉ ነበር። ከዚህ አንጻር እኛን በማናቸውም ነገር ላይ ፊርማችንን እንድናኖር ማድረግ መቻል እንደ ትልቅ ድል ነው የሚያስቡት።

**በጠቅላላው ግብጾች ይህንን ስምምነት ለመፈረም ባይፈልጉም እንኳን ኢትዮጵያ መስማማቷ ለሌላ ሴራቸው የሚመቻቸው መስሏቸው ይህንን ከፈረመች ሌላውንም ትቀበላለች በሚል ነው ፊርማ ውስጥ የገቡት**

በመሆኑም ይህ ስምምነት ሲፈረም የራሱ ድክመት ቢኖርበትም ለኢትዮጵያም መጠነኛ እውቅናን የሰጠ ነው። ነገር ግን መጀመሪያ የነበረበትን ዓላማ ስቶ ከፍላጎታቸው ውጭ ሄዷል። በዚህም ሲጀምሩት በነበረው ሁኔታ ማጠናቀቅ አልቻሉም።

እውነት ለመናገር የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድኖች ይህንን የመሰለ ሴራ ማክሸፋቸው በጣም ትልቅ ነገር ነው። እዚህ ላይ ባብራራው አንደኛ ሕጋዊ መሠረትን እንዳይዙ አድርገናቸዋል፤ አስገዳጅ ነገሮቹም ያን ያህል ጠንካራ አልሆኑም፡፡ በዚህም እነሱ ሊያደርጓቸው ለሚፈልጓቸው ነገሮች መሳሪያ ሊሆንላቸው አልቻለም።

በጠቅላላው ግብጾች ይህንን ስምምነት ለመፈረም ባይፈልጉም እንኳን ኢትዮጵያ መስማማቷ ለሌላ ሴራቸው የሚመቻቸው መስሏቸው ይህንን ከፈረመች ሌላውንም ትቀበላለች በሚል ነው ፊርማ ውስጥ የገቡት። ነገር ግን ቀጥሎ የመጣው የድርድር ሂደት ግን ኢትዮጵያ ወጥመዱ ውስጥ ስላልገባችላቸው ስምምነቱ ጥቅም አልባ ለመሆን ችሏል።

በዚህ ስምምነት አልሳካ ሲላቸውም የአሜሪካን መንግሥት አስተዳደርን በማግባባት ኢትዮጵያን ማስገደድ ውስጥ ገቡ፡፡ በጸጥታው ምክር ቤት በኩል መግባትና የመሳሰሉትን ተግባራት ቢፈጽሙም እስካሁን ድሉ የኢትዮጵያ ከመሆን አላለፈም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሕዳሴውን ግድብ ጉዳይ በቅርበት እንደሚከታተል ዜጋ እስከ አሁን የመጣንበትን የድርደር ሂደት ጠቅለል አድርገው ሲመለከቱት ምን ዓይነት ሥዕል ይፈጥርቦታል?**

**አቶ ግርማ ፡-** ለእኔ ሀገሬ ብዙ ዓለም አቀፋዊ የድርደር ልምድ የሌላት ከመሆኑ አንጻር ትልቅ ትምህርት እንደ ሀገር ያገኘንበት ሆኖ ይሰማኛል። ሀገራችን በታሪኳ እንደዚህ ዓይነት ድርደር ውስጥ ገብታ የማታውቅ እንደመሆኗ ይህ ሂደት በጣም ትልቅ እንዲሁም ተግባራዊ ልምድ የቀሰምንበት ነው።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ኢትዮጵያ በድርድሩ ላይ...

ከ ገጽ 9 የዞረ



በሌላ በኩል ልምድ መቅሰሙ ትምህርት ማግኘቱ እንዳለ ሆኖ ብዙ ጊዜ የባከነበት ነው። ይህንን ያልኩበት ዋናው ምክንያት ድርድር የሁለት ወገኖችን ፍቃደኝነት የሚፈልግ ነው። እነሱ ግን በውስጣቸው ተንኮል ሴራ ይዘው የሚመጡ ከመሆናቸው አንጻር ስናየው የባከነ ጊዜም ሆኖ ይሰማኛል። ያም ሆነ ይህ ግን ድርድሩ ሂደቱ አሰልቺና ጊዜ ጨራሽ ቢሆንም እኛ ደግሞ የግድብ ግንባታ ሥራችንን ጎን ለጎን የሰራንበት በመሆኑ አትርፈናል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በድርድሩ ላይ የአካሄድ ለውጥ ማድረግ አለባት የሚሉ ወገኖች አሉ፤ በዚህ ላይ እርስዎ ምን ይላሉ ?**

**አቶ ግርማ ፡-** ይህ በጣም ጥሩ ነጥብ ነው። ኢትዮጵያ አሁን ላይ በድንበር ተሻጋሪ የውሃ ድርድር ላይ በቂ ትምህርትና ልምድ ወስዳለች፤ ከዚህ ቀጥሎ የስትራቴጂ ለውጥ ማድረግ በጣም ያስፈልጋታል። አሁን ባለው ሁኔታ እነሱ ሲፈልጉ ይቀላቀላሉ ካልፈለጉ ይተውታል፡፡ በዚህ መንገድ መቀጠል አዋጭ አይደለም። በነገራችን ላይ አሁን በሰሞኑ ድርድር ስብሰባ ረግጠው ሲወጡ ምናልባትም ለአራተኛ ጊዜያቸው ይመስለኛል። በመሆኑም በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ አዋጭ ባለመሆኑ አሁን ላይ የድርድር አጀንዳችንን መቀየር ይገባናል።

የድርድሩ አጀንዳ ቢሆን ብዬ የማስበው በሁለት ነገሮች ላይ ነው። አንደኛው በተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ በተጨባጭ እየሆነ ያለው ነገር ምንድን ነው፤ ግብጽ ምን እያደረገች ነው? የሚለውን አይቶ አቅጣጫን ማሳመር ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ ብነግርሽ ግብጽ እኤአ ከ2021 ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የግብርና ልማት በመላ ሀገሪቷ እየሰራች ነው። በዚህም በረሃውን ከ45 ኪሎ ሜትር በላይ በማቋረጥ በሰው ሠራሽ ውሃ መተላለፊያ በመጠቀምና ሐይቅ በመስራት ከፍ ያለ የልማት ሥራን እያከናወነች ትገኛለች። ይህ እንግዲህ የሚሰራው የሌሎች ሀገሮችን ጠይቃ ይሁንታን ሳታገኝ ፤ ስምምነት በሌለበት የተፋሰሱ ሀገሮች በውሃ አጠቃቀማቸው ላይ ተጨባጭ የሆነ ውሳኔ ላይ ሳይደርሱ የምትሰራው ሥራ ነው።

በአንጻሩ ግን ይህንን ሁሉ ጊዜ የደረሰ ድርድርና ንግግር እየተደረገ ያለው ኢትዮጵያ ሳታማክረንና ሳታስፈቅደው ግድብ ገነባች የሚል ነው። የእኛ ግድብ ግን ኤሌክትሪክ አመንጭቶ መሄድ ነው ሥራው፤ ውሃን አናስቀርም፤ እነሱ ግን ከዚህ አልፈው የውሃ እጥረት እያለ ሌሎች ሀገሮች መጠቀም ሳይጀምሩ እየተሽቀዳደሙ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመሥራት ነገ ለሚያነሱት ቅድሚያውን የያዝነው እኛ ነን ለሚለው ሃሳባቸው መደላድል እየፈጠሩ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እየሰሩ ያሉት ሥራ ሕገ ወጥ ነው፤ ምክንያቱም ውሃውን መጠቀም የሚችሉት እዛው ተፋሰሱ ዙሪያ እንጂ አውጥቶ መጠቀም ሕጉ አይፈቅድላቸውም።

ለምሳሌ እኛ እንጦጦ ተራራን ቆፍረን ዓባይን ወደዚህ እንዲፈስ ማድረግ እንችላለን፤ ነገር ግን ይህ አካሄዳችን ከተፋሰሱ ሕግ ውጭ ስለሚያወጣን አልፎም በዓለም አቀፍ ሕጎች ጥያቄ ስለሚያስነሳ ይህንን ማድረግ አንችልም፡፡ ግብጾች ግን በማናለብኝነት እየሰሩ ያሉት እሱ ነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ግብጽ ውስጥ “ቶሺካ ዲፕረሽን” የሚባል አለ። ሥራው ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከፍተኛ የሆነ የልማት ማስፋፊያ ሥራ እየተከናወነ ነው። ለዚህ ሥራ ውሃ እየተጠለፈ የሚወጣው ደግሞ ከናስር ግድብ ላይ ነው። ይህ አካሄድ ደግሞ ሕገ ወጥ ነው፡፡

የሌሎች ሀገራት እርሻዎችንም በአሁኑ ወቅት ትልቅ በጀት መድበው እየሰሩ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ሲጠቃለል ግብጾች አሁን ላይ እያከናወኗቸው ያሉት ፕሮጀክቶች የሕዳሴውን ግድብ እጥፍ እንደውም ሁለት ሕዳሴ የሚያህል ነው። ውሃው ደግሞ ከግድቡ አውጥቶ ወደሌላ አቅጣጫ አዙሮ የግብርና ሥራን ለማስፋፋት ማለት ነው።

**እንጦጦ ተራራን ቆፍረን ዓባይን ወደዚህ እንዲፈስ ማድረግ እንችላለን፤ ነገር ግን ይህ አካሄዳችን ከተፋሰሱ ሕግ ውጭ ስለሚያወጣን አልፎም በዓለም አቀፍ ሕጎች ጥያቄ ስለሚያስነሳ ይህንን ማድረግ አንችልም፡፡ ግብጾች ግን በማናለብኝነት እየሰሩ ያሉት እሱኑ ነው**

እንደዚህ ዓይነት ሕገወጥነት ከመስፋፋቱ አንጻር እኛ ማድረግ ያለብን በሕዳሴው ግድብ መጨቃጨቅ ሳይሆን እያደረጉ ያሉት ሕገወጥ ተግባር ያቁሙ ማለት መቻል ነው። ይህ ውሃን ከተፈጥሯዊ ጉዞው አውጥቶ የመቀራመት ነገር ተጠያቂነት እንደሚያስከትል ማወቅ አለባቸው።

በመሆኑም ኢትዮጵያ የውሃው ምንጭ እንደመሆኗ ሕጋዊ ጥያቄን መጠየቅ መቻል አለባት። በተፋሰሱ ውስጥ እየተካሄደ ያለው የውሃ ብክነት ግብጽ እያካሄደችው ያለው ሕገ ወጥ ርምጃዎች በባለሙያ በተጠና ሁኔታ ጥያቄ ሆነው ሊነሱ ይገባል። እንደ ባለመብት እኛ አጀንዳ ተቀባይ ብቻ ሳንሆን አጀንዳንም ፈጣሪ የመሆን አቅማችን ሊጠናከር ይገባዋል። በድርድር መድረኩ ላይም ተጽዕኖ ማሳደር የምንችለው እኛ የራሳችንን አጀንዳ ይዘን መቅረብ አዳዲስ ሃሳቦችን ማመንጨት ስንችል ብቻ ነው። በጠቅላላው ከተከላካይነት ወጥተን ወደአጥቂነት መሸጋገር አለብን።

በመሆኑም ከዚህ በኋላ እኛ እንደ ሀገር ማድረግ ያለብን የአካሄድ ለውጥ ነው። እስከ አሁን ለግብጽ ጥያቄዎች መልስና ማስረጃ እየሰጠን 11 እና 12 ዓመት ከንቱ ጊዜን አባክነናል። ከዚህ በኋላ ግን ግብጽ እኛን በጥያቄ ወጥራ ይዛ ምን እያከናወነች እንዳለች? በውሃ እየተጫወተች መሆኑን መረጃዎችን ማሻተትና መፈለግ አስጠንተንም ለግብጾች እራስ ምታት መሆን መቻል አለብን።

አሁን ላይ ግብጾች የምግብ ምርት ፍላጎታቸውን ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ በሀገር ውስጥ ለመሸፈን ከፍተኛ ሥራን እየሠሩ ነው፤ በዚህም ከዓሣ ጀምሮ ጥራጥሬዎችን አትክልትና ፍራፍሬን በማምረት አስገራሚ ግስጋሴ ላይ ከመድረሳቸውም በላይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡትን ፍጆታ ቀንሰው ወደውጭ የሚልኳቸውን ምርቶች በመጨመር ላይ ናቸው። ይህ መልካም የሚሆነው በራሷ ሀገር ላይ በሚፈስ ወንዝ ቢሆን ነበር፤ አሁን ግን ከእኛ በሚመጣ ውሃ የተፋሰሱን ሀገራት ሳያማክሩ መጠቀም ግን ትልቅ ወንጀል ነው፡፡ በጠቅላላው እኛም እንደ ሀገር በፍጥነት የስትራቴጂ ለውጥ ያስፈልገናል።

ከዚህ ቀደም እኤአ በ2015 የተፈረመውን ስምምነት እስከ አሁን አራት ሀገሮች ፈርመው በሀገራቸውም ሕግ አድርገውታል፤ በመሆኑም አሁን ላይ ያልፈረሙ ሀገራት እንዲፈርሙ በማድረግ እንደ ተቋም ዳግም እንዲደራጅና ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ እንዲወጣ በተለይም እኛ ቀድመን መሥራት አለብን። ምክንያቱም በተፋሰሱ ውስጥ ትልቁን ውሃ አበርካቾች እንደመሆናችን።

**የተፋሰሱ ሀገራትም ተባብረው የጋራ ፕሮጀክቶችን እየሰሩ ወንዙንም የተፈጥሮ ጉዳት እንዳይደርስበት በመንከባከብ ግንኙነታቸውን ማጠናከርና ሌሎች ግንኙነቶቻቸውን ለማሳደግ ቢጠቀሙበት ጥሩ ነው**

ሌላው ውሃ የሚጋሩ ሀገሮች ውሃውን በፍትሃዊነት መከፋፈል መቻል ይኖርባቸዋል። በዚህም ሱዳንና ግብጽ ብቻ ተካፍለውት ያለው የውሃ መጠን በተፋሰሱ ሀገሮች መካከል እንዲሰፋ የሚያደርገውን አጀንዳ ወደ ድርድሩ ማቅረብ ይኖርብናል። ይህ ደግሞ እነሱ በጣም የማይፈልጉትና የሚፈሩት ጥያቄ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ዋና አጀንዳ ሆኖ ወደመድረኩ ሊመጣ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ጉዳዩን በቅርበት እንደሚከታተል ዜጋ ቢሆን ብለው የሚመኙትስ ነገር ምንድን ነው?**

**አቶ ግርማ፡-** በነገራችን ላይ የዓባይ ውሃ የግጭት የንትርክ የተንኮልና የሴራ ምንጭ ከሚሆን የልማትና የትብብር መንገድ ቢሆን ኖሮ ብዙ የተፋሰሱን ሀገራት በእድገት እንዲመነጠቁ የሚያደርጉ ስኬቶች ይመጡ ነበር። ወደፊትም ውሃውን የልማት፤ የእድገት የሌሎች ትብብሮቻችን ሁሉ መነሻ እርሾ ብናደርገው ምኞቴ ነው።

የተፋሰሱ ሀገራትም ተባብረው የጋራ ፕሮጀክቶችን እየሰሩ ወንዙንም የተፈጥሮ ጉዳት እንዳይደርስበት በመንከባከብ ግንኙነታቸውን ማጠናከርና ሌሎች ግንኙነቶቻቸውን ለማሳደግ ቢጠቀሙበት ጥሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ግርማ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## በኪሮሽ የሚሰሩ የክር አልባሳት ዲዛይነር

**ሰሚራ በርሀ**

ኢትዮጵያውያን ክርን በመጠቀም በእጅ ለሚሰሩ የሹራብ አልባሳት አዲስ አይደለንም። ከመዘነጫነት ባለፈ እናቶቻችን የቤት እቃዎቻቸውን ለማስዋብ ኪሮሻቸውን (ጥበቡን ለመሥራት የሚጠቅሙበትን መሳሪያ) ተጠቅመው፣ ሹራቦችን በተለያዩ ዲዛይኖች ይሰራሉ። ሙያውን ከራሳቸው አልፎ ለልጆቻቸው ያስተምራሉ። ይህ የእጅ ሥራ ጥበብ ውጤት ዘመናትን የተሻገረ የኢትዮጵያውያን መገለጫ ነው።

አሁን አሁን ደግሞ በክር በሚሰሩ የሹራብ አልባሳት በፋሽን ኢንዱስትሪው በስፋት ተፈላጊ እየሆኑ መጥተዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለሙያው ፍቅር ያላቸው ወጣቶች በኪሮሽ የሚሰሩ የሹራብ አልባሳት ሥራን እያስተዋወቁ ይገኛሉ። በተለይ በክር የሚሰሩ የሹራብ አልባሳት የብዙዎችን ቀልብ እንዲስብ እያደረጉ ናቸው።

ወጣት የአምላክ ፍቃዱ ትባላለች። በፋሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ በእጅ ሥራ ውጤቶች ማምረት ሙያ ላይ ተሰማርታለች። በባህሪዋም ለየት ያሉ አልባሳትን ታዘወትራለች። ከዚህ ፍላጎቷ በመነሳት የእጅ ሥራ ውጤት የሆኑ በተለያየ ዓይነት ክር የሚሰሩ ልብሶችን በእጇ በመሥራት ለገበያ ታቀርባለች። አልባሳቱን ዲዛይን አድርጋና ሰርታ ከማቅረብ ባለፈ ሙያውንም ፍላጎት ላላቸው ሰዎች ታስተምራለች። ኪያ የእጅ ሙያ ማሰልጠኛ በሚል ትምህርት ቤትም ከፍታለች። ማሰልጠኛው በዘርፉ የመጀመሪያው መሆኑንም ነው የምትገልጸው።

ወጣት የአምላክ በክር የሚሰራ የእጅ ሙያውን የተማረችው ተማሪ በነበረችበት ወቅት ነው። በትርፍ ጊዜዋ በበይነ መረብ ላይ የሚገኙ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማየት ነበር ራሷን በሂደት ያስተማረችው። የምትሰራቸውን ልብሶች በቅርቧ ያሉ ሰዎችና ቤተሰቦቿ መውደድ እንደጀመሩ የምትገልጸው የአምላክ፣ የእጅ ሥራዎቿን ከራሷ አልፎ ለሌሎች ሰዎች ጭምር በስጦታ መልክ ትሰጥ እንደነበርም ታስታውሳለች።

የአምላክ በክር በሚሰሩ የእጅ ሥራ አልባሳት ላይ ያላትን



በክር የሚሰሩ የእጅ ሥራ አልባሳት ተፈላጊነት እየጨመረ ነው

ችሎታ በተለያየ ጊዜ ብታዳብረውም ወደ ገበያ ለማቅረብ ግን ሃሳቡ አልነበራትም። ትምህርቷን ያጠናቀቀችው በማርኬቲንግ ሲሆን ተቀጥራ በምትሰራባቸው ቦታዎች ላይ በትርፍ ጊዜዋ እነዚህን የክር አልባሳት ትሰራለች። ይህንን የተመለከቱ ወደ ቢሮዋ የሚመጡ ሰዎችም ሥራዋን መውደድ ይጀምራሉ፤ ይህ ብቻም ሳይሆን እንድትሰራላቸው ጥያቄ ያቀርቡላት ጀመር። ያን ጊዜ ነው የተለያዩ ትዕዛዞችንም ተቀብላ መሥራት የጀመረችው።

በብዛት ትእዛዝ መቀበል የጀመረችውና ገበያውን የተቀላቀለችው በኮሮና ወረርሽኝ ወቅት ነበር። በጊዜው የተለያዩ ማህበራዊ ገጾችን በመጠቀም ትእዛዝ መቀበልና ሽያጭ ማከናወኑን ቀጠለችበት።

የአምላክ ክሮችን በመጠቀም አልባሳቱን በተለያዩ ቀለሞችና የክር ዓይነቶች ዲዛይን አድርጋ የምትሰራ ሲሆን፣ በዚህም ጋወኖችን ፣ ሹራቦችን፣ ሱሪዎችን፣ የብርድ መከላከያ ስካርፎችን፣ ኮፍያዎችን እና ሌሎች አልባሳትን እያመረተች ለገበያ ታቀርባለች። በተለይ በብዛት ለሴቶች የተለያዩ አማራጮች ያሏት ሲሆን ፣ ለወንዶች እንደ ሹራብ ዓይነት አልባሳት ተፈላጊ መሆናቸውን ትናገራለች። በሌሎች ሀገራት በጣም የተለመዱና በኛ ሀገር ግን ብዙም ያልታወቁ ዲዛኖችን ክርን በመጠቀም መሥራት እንደሚቻል ገልጻለች።

የአምላክ እንደምትናገረው፤ ክርን በመጠቀም የተለያዩ አልባሳትን መሥራት ይቻላል፤ የበጋ ወቅት በሚሆንበት ጊዜ ቀለል ያሉ አላባሽ ልብሶች ፣ ቀሚሶች የምትታዘዝ ሲሆን፣ በክረምት ወቅት ደግሞ ክርም በባህሪው ስለሚሞቅ ጋዋን፣ ሹራብ ፣ ለብርድ የሚሆኑ ልብሶች ትእዛዝ ይቀርብላታል። በክር ከሚሰሩ ልብሶች በጣም የሚወደዱት ጋወኖች እና በተለምዶ ቶፕ የሚባሉት ከላይ የሚለበሱ ልብሶች ናቸው።

እነዚህን የእጅ ሥራዎቿን በተለያዩ የማህበራዊ ገጾች እና በምታውቃቸው ሰዎች አማካኝነት ታቀርባለች። በመቀጠልም በተለያዩ ባዛሮች ላይ በመሳተፍ ሥራዎቿን ማስተዋወቅና በሰፊው መሸጥ የሚያስችላትን ዕድል አገኝታለች።

የምትሳተፍባቸው መድረኮች በአብዛኛው የውጭ ሀገር ዜጎች የሚሳተፉባቸው መሆናቸውን ጠቅሳለች። እነርሱ ለእጅ ሙያ ትልቅ ቦታ እንደሰጡ ገልጻ፣ ከእነርሱ የምታገኘው ማበረታቻ እንደጠቀማት ትናገራለች። በሀገር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችም በአሁኑ ወቅት በኪሮሽ ለሚሰሩ የእጅ ሥራ አልባሳት ያላቸው አመለካከት እየተቀየረ መምጣቱን ገልጻለች። ይህም በዚህ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ ሰዎችን እንደሚያበረታታም ነው የተናገረችው ።

የአምላክ የምትሰራቸው አልባሳት ተፈላጊ ቢሆኑም ለመሥሪያ የሚሆኑ የክር ግብዓትና ሌሎች ቁሳቀስ በሀገሪቱ አለመኖሩ እንደ ተግዳሮት እንደሆነባት ጠቁማለች። ሌላው እንደ ምክንያት የምታነሳው ጉዳይ በሀገር ውስጥ የሹራብ ክር ተብለው የሚሸጡት ጥራታቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን ነው። በተለምዶው የዳንቴል ክር የሚባለውን ለመጠቀም ደግሞ የአልባሳቱን ጥራት ይቀንሳል ትላለች። እሷ ግን ጥራታቸውን የጠበቁ ክሮችን ከውጭ በማስመጣት እንደምትሰራ ጠቅሳ፣ ለግብዓት እጥረቱ መፈጠር እንደ ምክንያት የሚነሳው በስፋት በክር የሚሰሩ አልባሳት መጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ አለመሆኑ ነው ትላለች። አቅራቢዎች ላይ ችግር እንዳለም ጠቁማለች።

እሷ እንዳስታወቀችው፤ ጥራት ያላቸው የክር ዓይነቶች ዋጋቸው ውድ በመሆኑ ምክንያት የእጅ ሥራ ባለሙያዎች በዚያ ዋጋ ገዝተው ለመሥራት እና መልሰው ለደንበኞቻቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ ይቸገራሉ። የኢንዱስትሪው ትልቁ ፈተና በተመጣጣኝ ዋጋ የግብዓት አቅርቦት ማግኘት አለመቻል ነው።

የአምላክ የክር አልባሳት በመሥራት በማህበራዊ ድህረ ገፅ ማስተዋወቅ በመጀመሯ ምክንያት ምርቶቿ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ነው። ወደ ሙያው የሚገቡ ዲዛይነሮችም እንዲሁ እየተበራከቱ መጥተዋል። በማሰልጠኛ ተቋሙ የሚማሩትም በርክተዋል። በተለይ ትርፍ ጊዜያቸውን ተጠቅመው ተጨማሪ ሙያ የሚፈልጉ ሰዎች የእሷን ትምህርት ቤት ተመራጭ እያደረጉት ይገኛሉ።

‹‹በአሁኑ ሰዓት ከኪሮሽ ሥራ ውጭ የሻማ አሰራር፣ የቤት ውስጥ የግድግዳ ጌጦች የሚያስተምሩ አምስት ባለሙያዎች አሉን። በኛ ተቋም ተምረው የግላቸውን ሥራ የጀመሩ ሰዎችም አሉ›› የምትለው የአምላክ፤ ከራሷ አልፋ ለሌሎች የሥራ እድል መፈጠር መቻሏን ትገልፃለች።

በእጅ ሥራ ሙያ ላይ ያለንን አመለካከት በመቀየር ይበልጥ ትኩረት አድርገን ብንሰራ ከዚህ የተሻለ ውጤት ማምጣት እንችላለንም ትላለች። ይህ ዘርፍ ገና ያልተነካ መሆኑን ጠቅሳ፣ በርካታ ወጣቶች በሙያው ላይ ቢሰማሩ የተሻለ የገቢ ምንጭ መፍጠር እንደሚችሉ ጠቁማለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ግርግር የሚፈጥሩ አስተባባሪዎች

**ዋሲልኝ አየለ**

ባለፈው ሐሙስ ማታ የመንግሥት ሠራተኞች መውጫ ሰዓት ላይ ነው። ከፒያሳ የሚነሳ የመንግሥት ሠራተኞች ማመላለሻ አውቶብስ (ፐብሊክ ሰርቪስ) ለመያዝ፤ በዚያውም እግሬን ላፍታታ ብዬ ከአራት ኪሎ ወደ ፒያሳ ሄድኩ። ብዙ ጊዜ መንገድ ላይ ስለሆነ የምይዘው ከመነሻው ምን እንደሚመስል አላውቀውም።

አውቶብሱ ተከፈተና አስተባባሪው ቀድሞ ገባ። ጊዜ ስላለው ነው መሰለኝ መታወቂያ የሚያየው የእያንዳንዱን ፊደል አቀማመጥ ሁሉ ይመስላል። መነሻ ስለሆነ እንጂ መንገድ ላይ የሚገቡት እኮ የታጠፈ 50 ብር ሁሉ ቢያሳዩት ልብ አይለውም። ያም ሆኖ ግን ጥንቃቄውን እያመሰገንኩ አልፌ ተቀመጥኩ።

የሰውየው ጥንቃቄ ግን ከአስተዋይነት የመጣ ሳይሆን ከግል አጉል ባህሪ የመጣ መሆኑን ያወቅኩት ቆይቼ ነው። በትንሽ ትልቁ ይጨቃጨቃል። ገና ሰርቪሱ ሳይነሳ ነው ከአንዱ ጋር ቀበቶ አላሰርሽም ብሎ የተጣላው። ማንም እንኳን ብዙ ሰው በሚጭኑ ትልልቅ አውቶቡሶች ውስጥ ተግባራዊ ባይደረግም ቀበቶ ማሰር ግዴታ መሆኑ ይታወቃል። የሰውየው ችግር ግን ግላዊ ባህሪ ነው። በመንገር ብቻ የሚያልቅን ነገር በቁጣ ይጀምራል። ትንሽ መልስ ከሰጡት ‹‹መታወቂያ አምጡ›› ይላል።

ይሄ የአንድ ተራ ግልፈተኛ ግለሰብ ባህሪ ስለሆነ ንቀን መተው እንችል ነበር፤ ዳሩ ግን ሌሎችም የዚህ ዓይነት ሰዎች በየአገልግሎት መስጫ ቦታው ስላሉ ሥርዓት እንዲኖራቸው ሊነገራቸው ይገባል።

በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ለጋራ ደህንነት ሲባል በየአካባቢው ነዋሪዎች ማታ ማታ ሰፈር ይጠበቅ በነበረበት ወቅት የነበረ ሁነት ትዝ አለኝ። በጠባቂዎችም ሆነ በነዋሪዎች ልክ ያልሆኑ እና አጉል ግርግር የሚፈጥሩ ድርጊቶችን አስታውሳለሁ። በጥንቃቄ መፈተሽ እና በጥንቃቄ መታወቂያ ማየት፣ በጥብቅ መመርመር እንዳለ ሆኖ፤ አንዳንድ ጊዜ ግን ልክ ያልሆነ ጥንቃቄ ደግሞ ሌላ ግርግር ይፈጥራል።

አንድ ዕለት ምሽት በየቤታችን ሳለን ድንገት ‹‹ያዘው! ያዘው! ያዘው....›› የሚል የብዙ ሰዎች ድምጽ ሰማን። ሁላችንም ከየቤታችን እየከፈትን ስንወጣ ግምታችን ለጥፋት የተዘጋጀ ሰው ተያዘ የሚል ነበር። የውጭውን በር ከፍተን ስንወጣ ሰብሰብ ብለው አንድ ከ30 ዓመት በታች ሊሆን የሚችል ወጣት እያናገሩ ነው። ራቅ ራቅ ያሉ ሰዎች የገሙቱት አለመከሰቱን ስላወቁ ነው መሰለኝ ይስቃሉ።

ነገሩን ስንጠይቅ፤ ጠባቂዎቹ ‹‹ያዘው! ያዘው!›› ያሉት ልጁ ለግል ጉዳዩ ሲሮጥ ሌላ ዓላማ ያለው መስሏቸው ነው። በዚያ ላይ መታወቂያ አሳይቶ በአጠገባቸው ያለፈ ልጅ ነው። ድጋሜ አገላብጠው ሲፈትሹት ምንም ነገር የለበትም። ‹‹ያዘው! ያዘው!›› ሲባል እሱም ግራ ገብቶት የሚያዘውን ሰው ለማየት ሲቆም ነው የያዙት።

ልጁ አስቸኳይ ጉዳይ ቢኖርበትም በዚያን ወቅት ባይሮጥ ጥሩ ነበር፤ የ20 ምናምን ዓመት ወጣት ግን ይህን ሁሉ አርቆ ላያስብ ይችላል። ግርግር የፈጠሩት ጠባቂዎቹ ናቸው። ልጁን ከጠረጠሩት ቀስ ብሎ በአንድ ሰው ድምጽ መጥራት ነው። ለደህንነት ሲባል ብዙ ሆነው መከተል ቢያስፈልግም ‹‹ጠብቀን ጠብቀን›› ብለውት ፈቃደኛ ካልሆነ ለሁሉም ነገር ያደርስ ነበር። ምንም በሌለበት ግርግር መፍጠር ግን ያልታሰበ አመቺ የግርግር ሁኔታ መፍጠር ነው። ያልታሰበ ግርግር ሲፈጠር ደግሞ ‹‹የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል›› ነው።

አንዳንዶቹ ደግሞ የመገላመጥ ምልክት ሳያሳይ አይቀርም በሚል መጠራጠር የሚጋጩም ነበሩ። ቢያጋጥም እንኳን ለወደፊቱ እንደዚያ እንዳያደርግ ነግሮ ቶሎ ማሰናበት ወይም በትህትና መምከር ሲገባ፤ እንደዚያ ዓይነት ሰው መገላመጥና ማስፈራራት ሌላ ግርግር መፍጠር ነው። እልህ ተጋብተው ድብድብ ቢፈጠር በእንደዚያ ዓይነት ወቅት አስደንባሪ ነው የሚሆነው።

አሁንም ቢሆን ያለንበት ወቅት ሙሉ ለሙሉ ነፃ ነው ማለት አይደለም። ከድብደባ እስከ ሞት ድረስ የሚደርሱ አደጋዎችን እየሰማን ነው። ለመደበኛ የፀጥታ አካላትም ሆነ የአገልግሎት አስተባባሪዎች መታወቂያ በትህትና ማሳየት፣ የሚጠይቁትን ሁሉ በተጠየቀው አግባብ መመለስ ያስፈልጋል። በዚያው ልክ ግን የፀጥታ አካላትም ሆኑ አስተባባሪዎች በግልምጫ እና በስድብ መጀመር የለባቸውም። ምክንያቱም በሥራቸው ላይ ግርግር ይፈጥራል።

አንዳንድ የፀጥታ አካላት ተጠያቂው አካል ምንም ዓይነት ማንገራገር ሳያሳይ በግልምጫ እና በቁጣ የሚጀምሩ አሉ። ወይም አንዳንድ ዜጎች ባለማወቅ የተከለከለ ነገር ሊያደርጉ ሲሉ እንደማይቻል መንገር ሲገባ በግልምጫ አለፍ ሲልም በጥፊና በእርግጫ የሚማቱ አሉ። ምንም እንኳን ግልምጫም ሆነ መደባደብ አግባብ ባይሆንም ቢያንስ ሰውየው እምቢ ካለ በኋላ አይሻልም? አንዳንዶቹ ለምን አላወቅክም በሚል ብቻ ሊማቱ ይችላሉ።

እንደ ዜጋ ቢቻል ሁላችንም መሰልጠን አለብን። ሁላችንም አስተዋይ መሆን አለብን። ይህ ግን እንኳን ገና ብዙ ለሚቀረን ለእኛ የበለጸጉ ናቸው ለሚባሉ ሀገራትም አይቻልም። ሁሉም ዜጋ አስተዋይ ይሆናል ማለት በፍፁም አይቻልም። ወጣ ያለ ባህሪ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ስለዚህ አስተዋይነትና ትህትና ሊያስተምሩ የሚገባቸው ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ናቸው። ምክንያቱም ለዚያ ኃላፊነት (አስተባባሪነት) የተመረጡት የተሻሉ ናቸው ተብለው ነው።

ለምሳሌ አንድ ተረኛ የሆነ ጠባቂ ወይም የሆነ አገልግሎት አስተባባሪ፤ አንድ የሰከረ ሰው አጋጠመው እንበል። የሰከረ ሰው ሊያደርጋቸው የሚችሉ ነገሮች ይታወቃሉ። ሊሳደብ ሁሉ ይችላል። ብልጠትና አስተዋይነት ማለት ከዚህ ሰው ጋር እልህ ሳይጋቡና ሳይገላምጡ ቀስ ብሎ እያሳሳቁና እያጫወቱ መፈተሽ ነው፤ መታወቂያውንም ማየት ነው። ከዚያ ውጭ ግን፤ ወደ ቁጣ እና ማደነባበር ከሄዱበት እንኳን የሰከረ ሰው ያልሰከረውም ግርግር ካልፈጠርኩ ሊል ይችላል። ምንም ዓላማ አስቦ ባይሆን እንኳን በጊዜያዊ ስሜታዊነት ወደ ሌላ ነገር ሊገባ ይችላል።

ያልታሰበባቸው በእልህ መጋባት ብቻ የተፈጠሩ ብዙ ግጭቶችን አስተውየ አውቃለሁ። ግጭቶች የተፈጠሩት በአንደኛው ወገን አላዋቂነትና አጉል ጀብደኝነት ነው። አንዳንድ ጊዜ በአስተባባሪ አንዳንድ ጊዜ በባለ ጉዳይ ግልፍተኝነት አለመግባባቶች ይፈጠራሉ። አንዳንዱ ባለጉዳይ (ተገልጋይ) ወይም መንገደኛ በግሉ ያጋጠመውን ችግር ሌላ ሰው ላይ ለመወጣት ያስባል። በመሆኑም እንደ ነዋሪ የሚጠየቃቸውን ሕጋዊ ግዴታዎች ሁሉ ‹‹ምን አገባችሁ!›› ይላል። አንዳንዱ የፀጥታ አካል ወይም አስተባባሪ ደግሞ ሥነ ሥርዓት ያለውን የሰለጠነ ዜጋ ሁሉ ሲጠይቅ በግልምጫ ሊሆን ይችላል።

በየቦታው ብዙ ዓይነት ባህሪ ያለው ሰው ቢኖርም ቢያንስ ግን ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች (ትንሽም ብትሆን) የተሻለ አርዓያ ሊሆኑ ይገባል።

# ለሩሲያ ኃያልነት ትልቅ አቅም የሆነው የሕዝቧ ትጋት!

ጌትነት ተስፋማርያም

በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች የተፈተነችው የሶቭየት ኅብረት እ.አ.አ. በ1991 ስትፈርስ ሩሲያ ሌላኛዋ የዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገር ሆና ቀጥላለች። የኃያልነቷ መገለጫ ዋንኞቹ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚዊ አቅሞቿ እንደሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ።

በመሬት ስፋቷ ከዓለም አንደኛ የሆነችው ሩሲያ የበርካታ ተፈጥሮ ሃብት ባለቤትም ነች። በተለይም ሩሲያ በዓለም በነዳጅ ዘይት ምርት ቀዳሚ ከሆኑት አገሮች አንዷ ስትሆን፤ በተለይ ለአውሮፓ በዋነኛነት የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ታቀርባለች።

እ.ኤ.አ. በ 2022 በሩሲያ ውስጥ ያለው የነዳጅ ዘይት ምርት 548 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ነበር፤ በቀን ከዘጠኝ እስከ 10 ሚሊዮን በርሜል በላይ ድፍድፍ ነዳጅ ታወጣ ነበር።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ሩሲያ አውሮፓ ከምትፈልገው የተፈጥሮ ጋዝ 40 ከመቶ የሚሆነውን ታቀርባለች። ይሁንና አሁን ላይ ሩሲያ ከዩክሬን ጋር በገባችው ጦርነት ምክንያት የአውሮፓ ኅብረት ለጣለው ማዕቀብ ምላሽ ለመስጠት፤ መጠኑን ቀንሳለች።

በወታደራዊ አቅሟ ግዝፈት የምትታወቀው ሩሲያ የኒኩሌር አረር ከታጠቁ ጥቂት ኃያላን ሀገራት ተርታ የምትሰለፍ ነች። ከወራት በፊትም “ግዙፍ” የኒውክሌር ጥቃት የማድረስ አቅሟን የሚፈትሽ ልምምድ ማከናወኗ የሚታወስ ነው።

ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ለሁለንተናዊ ዝግጁነት በሚል መርሕ የወታደሮቿን ቁጥር አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ለማድረስ ምልምላ እያከናወነች ነው። በባሕር ሰርጓጅ መርከቦችና በስለላ ድርጅቷ አማካኝነት እራሷን ለመጠበቅ በተጠንቀቅ ላይ ነች።

ይህ የወታደራዊ አቅሟ በኢኮኖሚውም በአግባቡ የተደገፈ ነው፤ በዓለም የስንዴ ምርት ታላቅ እምርታ ላይ ከመድረሷ ባሻገር በብረታብረትና በኢንዱስትሪ ምርቶች ወታደራዊ መሣሪያዎችን በሚያመርቱ ማዕከላቷ አማካኝነት ከበርካታ ሀገራት ጋር ጥብቅ ኢኮኖሚያዊ ቁርኝት ፈጥራለች።

ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት በማጎልበጽ ላይ ስትሆን፤ ከምሥራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያና ኤርትራ ጋር በተለያዩ የኢኮኖሚ አማራጮች ያላትን መስተጋብር በማጠናከር ላይ ትገኛለች።

ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ የሚዲያ አባላትም ይህችኑ ታላቅ ሀገር ለመጎብኘት ወደ ሩሲያ ተጉዘዋል፤ እኔም የቡድኑ አባል በመሆን ሀገሪቱን የመጎብኘት እድል አግኝቻለሁ። በዚያ የነበረኝን ቆይታም በወፍ በረር እንዲህ አቀርበዋለሁ።

### ሞስኮን እንደመግቢያ

በሞስኮ ዙሪያ አራት የአየር ማረፊያዎች አሉ። ከኢትዮጵያ፣ ከግብጽ፣ ከቱርክ፣ ከተለያዩ የዓረብና የእስያ ሀገራት የተውጣጣን ጋዜጠኞችም ሞስኮው ቭኖኮቮ በተሰኘው አየር ማረፊያ አድርገን ወደከተማዋ ዘለቅን። ከዜሮ በታች እስከ 12 ዲግሪ ሴልሺየስ የሚደርሰው የሞስኮ ቅዝቃዜ ኮፍያና የሹራብ ጓንት አድርገው እንኳን አጥንት ሰርስሮ የሚገባበት ኃይል አለው።

በመዲናዋ አውራ ጎዳናዎች በብዛት የሚታዩት ተሽከርካሪዎች ናቸው፤ እግረኞች እምብዛም ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ የከተማዋ ቅዝቃዜ ስለመሆኑ ለመገመት አይከብድም። ለከተማዋ መጠሪያ የሆነው ግዙፉ የሞስኮቫ ወንዝ እንኳን ወቅቱ በረዷማ በመሆኑ ረግቶ ተቀምጧል፤ በዚህ ምክንያት ፈጣን ጀልባዎች ከእንቅስቃሴ ተገትተዋል።

የፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን መቀመጫ ክሬምሊን ቤተ-መንግሥት ደግሞ ግርማውን እንደተላበሰ ይታያል። የሞስኮ ጥንታዊ ሕንጻዎች፣ በሥነ-ሕንጻ ውብታቸው የደመቁት አብያተ ክርስቲያናትና መስጂዶች፤ የሶሻሊዝምን ርዕዮተ-ዓለም የሚያንፀባርቁት ግዙፍ ሐውልቶች፣ የጠፈርተኛው ዩሪ ጋጋሪን የፑሽኪንና የተለያዩ ጸሐፊዎችን ማስታወሻ ሐውልቶች ለከተማዋ ድምቀት ናቸው።

በመንገድ ዳር የሚገኙ ነዳጅ ማደያዎች ደግሞ ባለቤት አልባ እስኪመስሉ ድረስ ዩኒፎርም የለበሱ ሰዎች አይታዩባቸውም። ምክንያቱ ደግሞ ማንም ነዳጅ መቅዳት የፈለገ አሽከርካሪ የገንዘብ ካርዱን አውጥቶ የሚፈልገውን ያክል ከቀዳ በኋላ በእራሱ ከፍሎ የሚሄድበት አሠራር በመተግበሩ ነው።



ከኖቮሮሲይስክ የስንዴ ማከማቻ ማዕከል ከፍተኛ የስንዴ ምርት ለተለያዩ ሀገራት ይሰራጫል

የሩሲያ ዋነኛ የኢኮኖሚ አቅም የሆነ የተፈጥሮ ጋዝ በመኖሪያና ንግድ ቤቶች ውስጥ ለኃይል ምንጭነት ስለሚውል በሞስኮ ሕንጻዎችና መኖሪያ ቤቶች አቅራቢያ የጋዝ ማስተላለፊያ መስመሮችን ማየት የተለመደ ነው። ይሄው ጋዝ በሚሰጠው ሙቀት ታግዘው በርካታ የሞስኮ ነዋሪዎች ሥራቸውን በተሻለ ቅልጥፍና ያከናውናሉ።

እኛም የሞስኮ ቆይታችንን ጋብ አድርገን ለዋናው ጉብኝት ወደወደብ ከተማዋ ሴንት ፒተርስበርግ ለማቅናት ተዘጋጀን። 635 ኪሎ ሜትሮች የሚዘልቀውን ጉዞ በፈጣኑ ሜትሮ ባቡር ተያያዝነው። ምቾትና ፍጥነትን የተላበሰውን የባቡር ጉዞ አራት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አጠናቀን ወደ ሆቴላችን ገባን።

### የትራክተር ማምረቻ ማዕከል

የሩሲያ መርከቦች ወደአውሮፓና የተለያ ሀገራት ምርቶችን ከሚያመላልሱባቸው ሰባት ዋና ዋና ግዙፍ ወደቦች መካከል የሴንት ፒተርስበርግ ወደብ አንዱ ነው። ወደቡ ከብረታ ብረት ምርቶች እስከ ነዳጅ ዘይት ይጓጓዝበታል።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የተወለዱት በዚችው የወደብ ከተማ ሴንት ፒተርስበርግ ነው። በከተማዋ የሚገኘውን ኮንስታንቲኖቭስኪ ቤተ-መንግሥት የሀገሪቷ መሪ በተለያዩ ጊዜያት እንግዶችን ለመቀበል ይጠቀሙበታል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተመራው የኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም በተዘጋጀው የሩሲያ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ሲሳተፍ ከሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር የተገናኙት በዚህችው ሴንት ፒተርስበርግ ከተማ በሚገኘው ቤተመንግሥት ነበር።

በባልቲክ ባሕር ላይ በፊንላንድ ባሕረ ሰላጤ ራስጌ የምትገኘው፤ በቀድሞ ስሞቿ ፔትሮጋርድ እና ሌኒንግራድ በመባል የምትታወቀው ሴንት ፒተርስበርግ ከእኛዋ አዲስ አበባ ጋር እህትማማች ከተማ ነች። እህትማማችነቱ በሁለቱ ከተሞች መካከል በሕዝብ ትራንስፖርት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በጤና፣ በትምህርትና በማኅበራዊ መስኮች በጋራ መሥራትን ዓላማ ያደረገ ነው።

የወደብ ከተማዋ ሴንት ፒተርስበርግ የፖለቲካና የንግድ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎችም መናኸሪያ ናት። የጋዜጠኞች ቡድኑም ዋነኛ የጉብኝት ማዕከል የሆነው ኪሮቬትስ የተሰኘው ትራክተሮችና የተለያዩ ማሽነሪዎች የሚመረቱበት ግዙፍ ማዕከል ነው።

የራሱ ብረት ማቅለጫና ማሽነሪ መገጣጠሚያዎች እንዲሁም ጠንካራ ሠራተኞች ያሉት ማዕከሉ የጦር መሣሪያዎችን እንደሚያመርት ታሪኩ ያስረዳል። የባቡር ሐዲድና የተለያዩ መርከቦችን የሚመረቱባቸውን ማዕከላት ትተን 200 ሔክታር ላይ ያረፈው የትራክተር ፋብሪካ መጎብኘታችንን ቀጠልን።

በዓመት አራት ሺህ 300 የተለያዩ የፈረስ ጉልበት ያላቸው ትራክተሮችን የሚገጣጠምበት ፋብሪካው የሞተር ክፍሉን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዷን ቡሎን ጭምር ያመርታል። 24 ሰዓት የሚሠራበት ማዕከሉ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይሉ ሠራተኞች እንዳሉት የጉብኝቱ አስተባባሪ ሩሲያዊቷ ኢቭጄኒያ ፓቭሊዩኮቫ አስረዳችን።

በሩሲያ የትራክተር ማምረቻ ታሪክ ቀደምት ከሚባሉት መካከል የሆነው ፋብሪካው ከሀገሩ አልፎ ለተለያዩ ዓለማትም ምርቱን ያቀርባል። ኢትዮጵያም ትራክተሮችን በመግዛት ከፋብሪካው ምርቶች ተቋዳሽ እንደሆነች ተነገረን። ኬንያ፣ ግብጽና ለተለያዩ ሀገራት ምርቶቹን እየተረከቡ የሚገኙ ተጨማሪ ሀገራት ናቸው።

**“በተለያዩ ማዕቀቦች የተወጠረችው ሩሲያ እራሷን በምግብ ከመቻል አልፋ ሌሎችንም ለመርዳት የቻለችው በሥራና በሥራ ብቻ ነው”**

እስከ 460 የፈረስ ጉልበት አቅም ያላቸውን ግዙፍ ትራክተሮች ይገጣጠማሉ። ከጥቃቅን የትራክተሩ ክፍሎች አንስቶ ግዙፉ ጎማውና ሙሉ ሲስተሙ በላብራቶሪ ፍተሻ ተደርጎበት ለአገልግሎት ይበቃል።

እያንዳንዱ የትራክተር ክፍል የሚመረትባቸው 500 ማሽኖች ኮምፒውተራይዝድ ሲስተም ተገጥሞላቸዋል። ከዚህ ባለፈ ፋብሪካው ቡልዶዘሮች እንዲሁም ለግግር በረዶ ማንሻ አሊያም ለአፈር መጋፊያ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎችን አምርቶ ለአገልግሎት ያውላል።

ፋብሪካው በ50 ቢሊዮን የሩሲያ ሩፐል ወጪ የማስፋፊያ ፕሮጀክት እያከናወነ ሲሆን፤ ምርቶቹን ከእጥፍ በላይ ለማሳደግ ውጥን ይዟል። ማዕከሉን ካየን ከአንድ ቀን በኋላ ደግሞ ታውራስ ፌኒክስ የተሰኘውን የተለያዩ የማሸጊያዎች ማሽኖች የሚገጣጠሙበትን ፋብሪካ የመጎብኘት ዕድል ገጠመን።

### የማሽን ማምረቻ ማዕከሉ

ከአንድ ሺህ 500 በላይ ዘመናዊ ማሽኖች ያሉት ፋብሪካው የብርጭቆ፣ የውሃና የተለያዩ ጭማቂዎች፣ የግሉኮስ መድኃኒት እንዲሁም የዱቄት ወተትና የተለያዩ አይነት የከረጢት ማሸጊያዎችን የሚያዘጋጁ ማሽኖችን አምርቶ ለአገልግሎት ያበቃል።

ማሽኖችን ለማምረት የሚረዱ የተለያዩ መሣሪያዎች ቅርጽ የሚወጣባቸው ሦስት የብረት ማቅለጫ ክፍሎች በዘመናዊ መልክ ተገንብተውለታል። በፋብሪካው ከሚመረቱ ማሽኖች አንዱ የለስላሳ መጠጦች ማሸጊያ ኮምፒተራይዝ ማሽን ይገኝበታል። ማሽኑ ጠርሙሶችን አምርቶ ጠርሙሶቹን አጥቦና አድርቆ መጠጦችን ለማሸግ የሚረዳ ነው፤ በደንበኞች ትዕዛዝ መሠረት ይመረታል።

የተለያዩ ቴክኒካል ሂደቶችን አልፈው ለገበያ የሚወጡ የማሸጊያ ማምረቻ ማሽኖች በገበያው ላይ ተወዳዳሪ መሆናቸውን የፋብሪካው የኤክስፖርት ክፍል ኃላፊ ኢቭጄኒ ቦንዳሬብ ገለጻ አደረጉ።

ፋብሪካው 800 ሠራተኞችን ይዞ በዓመት የተለያዩ መጠን ያላቸውን 900 ማሽኖች ያመርታል። እራሱን የቻለ የሜካኒካል ዲዛይን ክፍል ያለው ፋብሪካው በሮቦት ጭምር የታገዘ አሠራርን ተግባራዊ አድርጓል። ሁሌም ሥራ አለ፤ በምሳ ሰዓት እንኳን ሰዎች ይቀያየራሉ እንጂ የሚቆም ሥራ የለም።

ሩሲያኖች ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው። ኮስታራ ፊታቸው በሥራ ብቻ የተጠመደ ነው። የማሽን ማምረቻ ፋብሪካውን እንቅስቃሴ እየተዟዟርን ስንጎበኝ ማንም በአጠገባቸው ቢያልፍ ትኩረት ካደረጉበት ሥራ ለሰከንድ ዝንፍ እንደማይሉ ተመለከትን።

ቀጣዩ ጉዟችን ወደ ኖቮሮሲይስክ ከተማ ሆነ። ከአራት ሰዓታት የአየር በረራ በኋላ እ.አ.አ. በ2014 የክረምት ኦሎምፒክን በደማቅ ሁኔታ በማዘጋጀቷ ወደምትታወሰው ሶቺ ከተማ ደረስን። በሶቺ ጣፋጭ የዓሣና የአትክልት ምግቦችን ከቀማመስን በኋላ በአውቶቡስ የስድስት ሰዓታት ጉዞን በማድረግ በጥቁር ባሕር ዳርቻ በተቆረቆረችው ጥንታዊቷ ኖቮሮሲይስክ ከተማ ገብተን አረፍ አልን።

### የስንዴ ማዕከሏ ሌላኛዋ የወደብ ከተማ

ኖቮሮሲይስክ በአንጻራዊነት የተሻለ ሙቀት አላት፤ እንደሌሎች በረዷማ የሩሲያ ከተሞች አይደለችም። አምስት ዲግሪ ሴክሺየስ በሆነው የአየር ፀባይ ያለጓንትና ኮፍያ መንቀሳቀስ ይቻላል።

ከተማዋ ከፍተኛ የስንዴ ምርት ወደተለያዩ ሀገራት የሚጓጓዝበትን ወሳኙን ወደብ በጉያዋ ይዛለች። ከዚህ ባለፈ የኖቮሮሲይስክ የስንዴ ማከማቻ ማዕከል /ግሬይን ፕላንት/ በየቀኑ ለተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚላከውን ስንዴ ያጓጉዛል። እንደ ሩሲያ የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ከሆነ እ.አ.አ. በ2023/24 የምርት ዘመን ሀገሪቱ 135 ሚሊዮን ቶን የግብርና ምርት ትጠብቃለች፤ ከዚህ ውስጥ 90 ሚሊዮን ቶኑ የስንዴ ምርት እንደሚሆን ይገመታል።

ሩሲያና ዩክሬን በድምሩ ከአንድ አራተኛ በላይ የሚሆነውን የዓለም ስንዴ ወደ ውጭ ይልካሉ። ፕሬዚዳንት ፑቲንም ባዘዙት መሰረት ከ25 ሺሕ እስከ 50 ሺሕ ቶን የሚደርስ ስንዴ ለዚምባብዌ፣ ለቡርኪና ፋሶ፣ ለሶማሊያ፣ ለኤርትራ፣ ለማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክና ለማሊ እየተከፋፈለ ይገኛል።

ይሄው ስንዴ በዋነኛነት የሚጓጓዘው ከኖቮሮሲይስክ ስንዴ ማከማቻ ማዕከል ነው። ማከማቻ ማዕከሉ እያንዳንዳቸው ከ40 እስከ 100 ሺህ ቶን ምርት የሚይዙ የተለያዩ ዘመናዊ ጎተራዎች አሉት። ስንዴውን ከማከማቻው በአሳንሰር ተጠቅመው ወደመርከቦች የሚያጓጉዙ ከሰባት በላይ የባቡር መስመሮች አገልግሎት ይሰጣሉ። ሠራተኞች ድምጽ እንኳን ሳያሰሙ የዓለምን ትልቁን የስንዴ ምርት ያሰራጫሉ፤ ከሥራቸው ዝንፍ የለም።

ከማዕከሉ በዓመት ስምንት ሚሊዮን ቶን ምርት ወደተለያዩ ሀገራት ይላካል። በወር በአማካይ 25 መርከቦች ስንዴና የተለያዩ እህሎችን ጭነው በጥቁር ባሕር ላይ ጉዟቸውን ያደርጋሉ። የኖቮሮሲይስክ የስንዴ ማከማቻ ማዕከል /Novorossiysk Grain Plant, JSC/ የምርት ክፍል ምክትል ዳይሬክተር ሱትቼንኮ ኢቭጌኒይ እንደተናገሩት፤ ፕሬዚዳንት ፑቲን ባዘዙት መሠረት ወደኤርትራና ማሊ የሚጓጓዘው ስንዴ በመርከብ ላይ ነው።

የኖቮሮሲይስክ ወደብ በግዙፍ ጫኝ መርከቦች የተከበበ ነው። ትላልቅ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከወደቡ ወደተለያዩ ከተሞች እንቅስቃሴያቸውን ያደርጋሉ። በአጠቃላይ ከተማዋ የምርት እንቅስቃሴ የሚሳለጥባት ማዕከል ናት ቢባል ማጋነን አይሆንም።

እኛም የሩሲያን የኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች ጉብኝት አጠናቀን በመጣንበት አኳኋን ጥቁር ባሕርን አግድም እያየን ወደ ሶቺ ከተማ በአውቶብስ ጉዟችንን ተያያዝነው። በአሜሪካና አውሮፓውያን የተለያዩ ማዕቀቦች የተወጠረችው ሩሲያ እራሷን በምግብ ከመቻል አልፋ ሌሎችንም ለመርዳት የቻለችው በሥራና በሥራ ብቻ ነው።

ሩሲያኖች በዚያ በረዶ ለወራት በሚዘንብበት ምድር ላይ አይደለም ስንዴና የተለየዩ ሰብሎችን ማምረት ይቅርና መኖር በራሱ ከባድ በሚመስልበት የአየር ንብረት ጠንክረው በመሥራት ሀገራቸውን ለውጠዋል። በኢንዱስትሪ አብዮቱና በሕዋ ሳይንስ ምርምሩ እንዲሁም በሚሊታሪ አቅማቸውን እራሳቸውን በማጠናከር ከዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገሮች ተርታ መሰለፍ ችለዋል።

ይህ በራስ አቅም እራስን የመገንባት ምስጢር ታዲያ በእኛም ሀገር መሠረት ይይዝ ዘንድ እየተመኘሁ ከሶቺ ወደሞስኮ - ከሞስኮ ወደአዲስ አበባ የሚደረገውን በረራ ለመጀመር ተነሳሁ። በታላቅ ትግል አቅሟን ያስመሰከረችው ሩሲያ ዕውነትም የትጋት ተምሳሌት ነችና ኢትዮጵያውያን ከግዙፏ ሀገር ዜጎች ብዙ የምንማረው የሥራ ባህል አለ!

# ዓለም አቀፍ

## ከዓለማችን ምርጥ 10 ከተሞች መካከል ሶስቱ በካናዳ ይገኛሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ከዓለማችን ምርጥ 10 ለኑሮ ምቹ ከሆኑ ከተሞች መካከል ሶስቱ በካናዳ እንደሚገኙ መሆናቸውን የ'ግሎባል ሊቨቢሊቲ ኢንዴክስ' ጥናት አመለከተ።

የታዋቂው ኢኮኖሚስት ጋዜጣ አካልና ምርምሮችን እንዲሁም ትንተናዎችን የሚያዘጋጀው ኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት 'ግሎባል ሊቨቢሊቲ ኢንዴክስ' በየዓመቱ ለነዋሪዎች ምቹ የሆኑ ከተሞችን ደረጃ ያስቀምጣል።

ለዚህም የዓለማችን 173 ከተሞችን ገምግሞ ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን፣ በዘንድሮው ግምገማውም ከ10 ምርጥ ከተሞች ውስጥ ሦስቱ የካናዳ ከተሞች መሆናቸውን ይፋ አድርጓል። ካናዳ በምቹነት ዝርዝር ውስጥ ከአስሩ ሦስት ከተሞችን በማስመረጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዛለች።

ተቋሙ ከተሞቹን ሲመርጥ መስፈርት ያደረጋቸው መረጋጋት፣ የጤና ሥርዓት፣ ባህል እና ከባቢያዊ ሁኔታቸውን እንዲሁም የትምህርት እና የመሠረተ ልማት ሽፋንን በማጤን ነው።

የአውስትሪያዋ ቪየና፣ የዴንማርኳ ኮፐንሃገን የአውስትራሊያዋ ሜልቦርን ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይዘዋል።

ከአስሩ ምርጥ ከተሞች ውስጥ የተካቱት ሦስቱ የካናዳ ከተሞች ደግሞ ቫንኮቨር፣ ካልጋሪ እና መዲናዋ ቶሮንቶ ናቸው። ቫንኮቨር በአምስተኛ ደረጃ ስትቀመጥ፣ ካልጋሪ ከጄኔቫ ጋር ሰባተኛ ደረጃ እንዲሁም ቶሮንቶ ዘጠነኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።

ከተሞቹ ምርጥ በሆነ የጤና ሥርዓት እና ጥራት በተሞላው ትምህርት ሽፋን የሚታወቁ ሲሆን፣ ለእነዚህም አዎንታዊ ትሩፋቶች የመንግሥት ፖሊሲዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ካናዳውያን ይናገራሉ።

ሁለንተናዊ የሆነው የጤና አጠባበቅ ሥርዓት ካናዳን ለመኖሪያነት የተመረጠች ሥፍራ ያደርጋታል በማለት የቫንኮቨር ነዋሪ የሆኑት ሳማንታ ፋልክ ያስረዳሉ።

ልጄን ወደ ሆስፒታል ለመውሰድ ገንዘብ በሚያስጨንቅበት ሁኔታ ወይም የካንሰር ታማሚዎች ለመታከም ሙሉ ጥሪታቸውን በሚያሟጥጡበት ሀገር ውስጥ መኖርን አላስበውም ሲሉም እንዴት ካናዳ የጤና ሽፋን ሥርዓት ዜጎችን ያማከለ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚደረጉ ድጋፎች፣ አረጋውያን ለመደገፍ የሚደረጉ ጥረቶች እንዲሁም ትንንሽ የንግድ ሥራ ባለቤቶችን ለመደገፍ የሚደረጉ ጥረቶች የአገራችን መለያዎች ናቸው። ካናዳውያን ወዳጅነት በመመሥረት እና በመደጋገፍ ይታወቃሉ'' ይላሉ የቫንኮቨር ከተማ ነዋሪ የሆኑት እና ኦርጋናይዝድ ጄን የተሰኘ ሕይወት እና ንግድን የሚያደራጅ ድርጅት የሚመሩት ጄን ስቶለር።

ይህ የመደጋገፍ እና የወዳጅነት ስሜት ነዋሪዎች በግል እና በሙያዊ ሕይወታቸው የሚያድጉበት እንዲሁም ርካታ የሚያገኙበት አዎንታዊ ከባቢን ያበረታታል ይላሉ።

ካናዳ በሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እና ጎዳናዎች የምታፈሰው መዋዕለ ንዋይ በትልልቅ ከተሞቿ መጓጓዝን ቀላል ያደርገዋል። በካናዳ ከተሞች የግልዎት መኪና አያስፈልግዎትም።

ከተማዋ ውስጥ እንደፈለጉ የሚጓዙበት ባቡር፣ አውቶብስ በቀላሉ በየትኛውም ሰዓት፣ ቀን ተሌት ሳይሉ ያገኛሉ። በሞንትሪያል፣ ካልጋሪ እና ቶሮንቶ የኖሩት ሳማንታ እስከ 24 ዓመታቸው ድረስ መንጃ ፈቃዳቸውን አላወጡም ነበር። እንዲሁም የ53 ዓመት ጓደኛቸውም በቅርቡ መንጃ ፈቃድ ሊያወጡ እየተዘጋጀ ነው።

በተለይም ካናዳን ወይም ከተሞቹን ለነዋሪዎች ምርጥ እና ምቹ ያደረጋቸው ከቤት ወጥተው የሚዝናኑባቸው ሰፋፊ ፓርኮችን የከተማዋ ማዕከል ማድረጋቸው ነው።

"ሦስቱም እነዚህ ለኑሮ ምቹ የሆኑ ከተሞች ለተፈጥሮ ቅርብ መሆን ብቻ ሳይሆን በከተሞቹ ዲዛይን ውስጥም እንዲካተቱ ተደርገዋል'' ይላሉ ሳማንታ።

"በቶሮንቶ ውስጥ ነዋሪዎች የሚዝናኑባቸው በጫካ የተሞሉ ሸለቆዎች እንዲሁም የባሕር ዳርቻዎች አሉ። በሞንትሪያል በዛፍ የተሸፈኑ ጎዳናዎች እንዲሁም ሞንት ሮያል የተሰኘ ፓርክ አለ። ቫንኮቨር ደግሞ ከዓለም ምርጥ የከተማ የተፈጥሮ ሥፍራዎች ውስጥ አንዱ ምሳሌ የሆነው ስታንሊ ፓርክ አላት'' ሲሉ ሳማንታ ለቢቢሲ ያስረዳሉ።

ከተሞቹ ተፈጥሮን ማዕከል ባደረገ መልኩ ዲዛይን መደረጋቸውም ለነዋሪዎች የአዕምሮ እፎይታን ይለግሳሉ።

ሦስቱም የካናዳ ከተሞች የየራሳቸው ልዩ የሆነ ነገር ያላቸው ሲሆን፣ አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ለነዋሪዎች ባላቸው ምቹነት ነው። ውብ በሆነው የካናዳ ምዕራባዊ ጠረፍ ላይ የምትገኘው ካንኮቨር በተፈጥሮ ሀብቷ የታደለች ናት።

በምዕራባዊ አልበርታ ግዛት የምትገኘው ካልጋሪ በታዋቂዎቹ ሮኪ ተራሮች አቅራቢያ ትገኛለች። ነዋሪዎች ካልጋሪን ሲገልጿት ትልቅ ከተማ ብትሆንም እንደ ትንሽ መንደር አቃፊ የሆነች ይሏታል። የኑሮ ውድነቷም ከሌሎች ከተሞች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው።

የካናዳዋ መዲና ቶሮንቶ በሕዝብ ብዛት ቢኖራትም ከ1500 በላይ ፓርኮችን በመክፈት ነዋሪዎች ከቤታቸው ወጥተው መንፈሳቸውን የሚያድሱበት መንገድንም ቀይሳለች።

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የፓራሊምፒክ የብሔራዊ ቡድን ማጣሪያ ውድድር ተካሄደ

**ዓለማየሁ ግዛው**

የ2024 የፓሪስ ፓራሊምፒክ ውድድር ሊካሄድ የወራት ዕድሜ ብቻ ይቀረዋል። ዓለም በጉጉት የሚጠብቀው ይህ ውድድር በሺዎች የሚቆጠሩ የፓራ ስፖርተኞችን ያሳትፋል። ከነዚህም ውስጥ ኢትዮጵያዊያን የፓራ ስፖርተኞች በውድድሩ ለመሳተፍ የሚያበቃ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ፌዴሬሽን ስፖርተኞቹ በውድድሩ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ነጥብ እንዲያገኙ የብሔራዊ ቡድን ማጣሪያን በማድረግ ሥራውን ጀምሯል። በመሆኑም በፓራሊምፒክ ለመሳተፍ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ላይ የሚሳተፉ ይሆናል።

ለዚህም የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ፌዴሬሽን ዱባይ በሚካሄደው የ2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ሚኒማ ማሟያ ውድድር የሚሳተፉ አትሌቶችን ለመለየት የማጣሪያ ውድድር አካሂዷል። ታኅሣሥ 12 እና 13 በአዲስ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በተካሄደው የማጣሪያ ውድድርም በተለያዩ የጉዳት ዓይነቶች አትሌቶችን ለይቷል። በሚኒማ ማሟያው ውድድር ኢትዮጵያን በፓራሊምፒክ ለመወከል የማጣሪያ ውድድራቸውን ያከናወኑ አትሌቶች ከዓመት በፊት ከተካሄደው የኢትዮጵያ ቻምፒዮና የተመረጡና በተጨማሪም ጥሩ ውጤት ያላቸው አትሌቶች መሆናቸውን ተጠቅሷል።

ዓለም አቀፍ ውድድሩ ዱባይ ፋዛ በምትባል ከተማ የካቲት ወር መጀመሪያ የሚካሄድ ሲሆን ግራንድ ፕሪ (Grand prix) ይባላል። ይሄም የፓራ ስፖርተኞች በፓራሊምፒክ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ሚኒማ



**በወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በተካሄደው የማጣሪያ ውድድር በተለያዩ የጉዳት ዓይነቶች አትሌቶች ተለይተዋል፣**

የሚያሟሉበት ነው። በመሆኑም በፓራሊምፒክ ለመሳተፍ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ባሉት 18 ወራት አትሌቶቹ ሁለትና ሶስት የሚኒማ ማሟያ ውድድሮችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። የተመረጡት አትሌቶች ይሄንንና ሌሎች የሚኒማ ማሟያ ውድድሮችን እንዲሳተፉና እንዲዘጋጁ ለማድረግ እንደሆነም ተገልጿል።

በማጣሪያው እስከ 7 የሚደርሱ አትሌቶች የተመረጡ ሲሆን መጨረሻ ላይ የተሻለ ሰዓትና ብቃት ያላቸው አትሌቶች እንደሚለዩም ተጠቁሟል። ለዚህም ቴክኒክ ኮሚቴው በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ልየታውን የሚደርግ ይሆናል። በአትሌቲክስ 1 ሺ 500፣ 8 መቶ ፣ 400፣ 5 ሺ ሜትር፣ ጦርና አሎሎ ውርወራ እንደተመረጡ የተጠቆመ ሲሆን ዓለም አቀፍ ሰዓታቸው ታይቶ ከየዘርፉ አንድ አትሌት ለማካተት ጥረት እንደሚደረግ ተጠቅሷል። በማጣሪያው ድንክዬ፣ ሙሉ ለሙሉ ዓይነ ስውር፣ ጭላንጭልና እጅ ጉዳት ያለባቸው አትሌቶች ተሳትፈዋል።

የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዶክተር ጊዮን ሴይፉ፣ የማጣሪያ ውድድሩ የተካሄደው በኢትዮጵያ ቻምፒዮና አትሌቶች በነበራቸው ውጤት ላይ ተመስርቶ እንደሆነ አስረድተዋል። በዚህም መሠረት ከየውድድሩ ከአንድ እስከ ሶስት የወጡትን እና ከዛ በኋላ ባሉት ጊዜያት ጥሩ ብቃትን ያሳዩ አትሌቶችን አካቶ መሆኑን ተናግረዋል። ይሄም የተደረገው አሰልጣኞች ያዩትንና የሚያምኑበትን አትሌት እንዲያወዳድሩ በመግባባት ነው። የቻምፒዮና ውድድር አዘጋጅቶ መምረጥ የሚቀል ቢሆንም ፌዴሬሽኑ ባለበት የበጀት እጥረት ምክንያት በፊት የተመረጡትንና የተወሰኑ አትሌቶችን በመጨመር ማጣሪያውን ማካሄዱን ጠቁመዋል።

ፕሬዚዳንቱ የተመረጡት አትሌቶች በዱባይ ለሚካሄደው ውድድር ዝግጅታቸውን እንደሚያደርጉ ጠቅሰው፣ ለዝግጅትና ለጉዞ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከዓለም አቀፉ ፌዴሬሽን በመጠየቅ እና ከተለያዩ ለጋሽ አካላት በሚደረግ ድጋፍ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን ገልጸዋል። ለዚህ ውድድርም 7 ሰው እንኳ ለማሳተፍ ቢታሰብ 10 ሺ ዩሮ ገደማ የሚያስፈልግ ሲሆን ወጪው የሌሎች ልዑካን ቡድንን ሳያካትት ነው። ለሁለተኛው የሚኒማ ማሟያ ውድድር 25 ሺ ዩሮ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚያስፈልግም ጠቅሰዋል። ይሄም ምንጩ ከየት እንደሆነ መልስ ያላገኘ ጥያቄ ሲሆን ድጋፍ እንዲደረግ ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጥያቄ ለማቅረብ መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በዚህም የተነሳ አትሌቶች በግላቸው ልምምድ እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን ይሄም እስከ ውድድሩ መጀመር ድረስ መሆኑን ጠቅሰዋል። አሰልጣኞች አትሌቶቹ በሚገኙበት ቦታ ሥልጠና መስጠትና የክትትል ሥራን በመሥራት አትሌቶቹን ለውድድሩ የሚያዘጋጁም ይሆንል ብለዋል።

ዓለም አቀፉ የፓራሊምፒክ ኮሚቴ የሚረዳው ገንዘብ በጣም ትንሽ ከመሆኑም በላይ የሚውለው ለታለመለት ዓላማ ብቻ ነው። ለእንደዚህ ዓይነቱ ውድድር ገንዘቡን መጠቀም የማይቻልና ኢትዮጵያ ከዛ በኋላ በሚኖሩት ዓለም አቀፍ ውድድርና ግንኙነቷ ላይ ችግር ይፈጥራል። በመሆኑም ሀገራት ለእንደዚህ ዓይነት ውድድሮች ወጪዎቻቸውን በመሸፈን ከኮሚቴው ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠር ይኖርባቸዋል።

ፌዴሬሽኑ ለፓሪስ ፓራሊምፒክ ውድድር ተሳትፎ ለመብቃት በርካታ በሮችን ቢያንኳኳም ምላሽ የሰጠው አካል ባለመኖሩ መንግሥት እንዲደርስለትም ጥሪውን አስተላልፏል። የፓሪሱ ውድድር ሲመጣ መንግሥት ድጋፍ ሊያደርግ የሚችል ቢሆንም ለዛ ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉ ብዙ ነገሮች መኖራቸውንም ተጠቁሟል። ከዚህ በፊት በነበረው ውድድር የተሳተፈችው አትሌት የወርቅ ሜዳሊያን ማስመዝገብ የቻለች ሲሆን በቂ ድጋፍና ዝግጅት ካልተደረገ ይሄ ውጤት ላይኖር እንደሚችል ፕሬዚዳንቱ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ